# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ
## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

ሰዋስው
ቃላት
መፃፍ
ሥነ-ጽሑፍ
መናገር
ማንበብ
ማዳመጥ

## 5ኛ ክፍል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# ለመፅሐፉ ሊደረግ ስለሚገባው የአያያዝ ጥንቃቄ

የመማሪያ መፅሀፋችሁ የትምህርት ቤቱ ንብረት ቢሆንም እንደራሳችሁ ንብረት መያዝ ይኖርባችኋል፡፡ እንዳይጠፋም ጥንቃቄ አድርጉ፡፡

1. መፅሐፉን በቀላሉ እንዳይበላሽ በጠንካራ ወረቀት ሸፍኑት፡፡
2. መፅሐፉን ደረቅና ቆሻሻ በሌለበት ቦታ አስቀምጡት፡፡
3. መፅሐፉን ለመጠቀም ስትፈልጉ እጃችሁን አፅዱ፡፡
4. በመፅሐፉ ሽፋንም ሆነ የውስጥ ገፆች ላይ በፍፁም አትፃፉ፤ ስዕሎችንም አትሳሉ፡፡
5. ለመፅሐፉ ገፅ መለያ ወይም ምልክት ስትፈልጉ ጠንካራ ወረቀት ወይምክር ተጠቀሙ እንጂ ገፁን አትጠፉ፡፡
6. በመፅሐፍ ውስጥ ያሉትን ገለጻዎች ወይም ስዕሎች ገንጥላችሁአታውጡ፡፡
7. የመፅሐፉ ሽፋን ወይም ገፅ ከተገነጠለ በማስትሽ አያይዙ፡፡
8. መፅሐፉ ቦርሳ ውስጥ ሲገባና ሲወጣ እንዳይጨማደድ ጥንቃቄአድርጉ፡፡
9. መፅሐፉን ለሌላ ሰው ስታውሱም ሆነ ስትዋሱ እንዳይቀደድ ጥንቃቄ አድርጉ፡፡
10. መፅሐፉን ስትገልጡት ሽፋንና ገፁ እንዳይገነጣጠል በጥንቃቄ ያዙ፡፡

# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

## 5ኛ ክፍል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# አማርኛ

## እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

## 5ኛ ክፍል

አዘጋጆች:-

አብነት ማሙዬ {B.A}

ፀጋነሽ ወልደጊዮርጊስ {M.A}

ኃይሉ ግርማ {B.A}

ገምጋሚዎች:-

ለዝና መንግስቴ {B.E.D}
ነፃነት ጥጋቡ {M.A}
ይሻሙ ጌራወርቅ {M.A}

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

ምዕራፍ አንድ ሐገራዊ ባህል ------------------------------------------------------1
ማዳመጥ----------------------------------------------------------------------1
መናገር ---------------------------------------------------------------------2
ማንበብ ---------------------------------------------------------------------3
መጻፍ ----------------------------------------------------------------------6
ምዕራፍ ሁለት አዕዋፍ ---------------------------------------------------------12
ማዳመጥ-------------------------------------------------------------------12
መናገር ------------------------------------------------------------------13
ማንበብ ------------------------------------------------------------------13
መጻፍ -------------------------------------------------------------------15
ምዕራፍ ሶስት የሕይወት ታሪክ--------------------------------------------------23
ማዳመጥ-------------------------------------------------------------------23
መናገር ------------------------------------------------------------------24
ማንበብ ------------------------------------------------------------------25
መጻፍ -------------------------------------------------------------------27
ምዕራፍ አራት የአየር ንብረት ---------------------------------------------------34
ማዳመጥ-------------------------------------------------------------------34
መናገር ------------------------------------------------------------------35
ማንበብ ------------------------------------------------------------------36
መጻፍ -------------------------------------------------------------------39
ምዕራፍ አምስት ቅርስ ሀብት ነው-- -----------------------------------------46
ማዳመጥ-------------------------------------------------------------------46
መናገር ------------------------------------------------------------------47

ማንበብ --------------------------------------------------------------------------------47
መጻፍ --------------------------------------------------------------------------------49
ምዕራፍ ስድስት ግብር ለሀገር ልማት -----------------------------------------------56
ማዳመጥ-----------------------------------------------------------------------------56
መናገር --------------------------------------------------------------------------57
ማንበብ --------------------------------------------------------------------------57
መጻፍ ----------------------------------------------------------------------------60
ምዕራፍ ሰባት አጥንት ----------------------------------------------------------------68
ማዳመጥ-----------------------------------------------------------------------------68
መናገር --------------------------------------------------------------------------69
ማንበብ --------------------------------------------------------------------------70
መጻፍ ----------------------------------------------------------------------------72
ምዕራፍ ስምንት የአመጋገብ ስርዓት-----------------------------------------------77
ማዳመጥ-----------------------------------------------------------------------------78
መናገር --------------------------------------------------------------------------79
ማንበብ --------------------------------------------------------------------------80
መጻፍ ----------------------------------------------------------------------------82
ዋቢ መጽሐፍት -------------------------------------------------------------------88-89

## መግቢያ

አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ በትምህርት የሚሰጥበት ዋና ዓላማ ተማሪዎች በቋንቋው የማድመጥና የማንበብ ክህሎት እንዲያዳብሩ፤ ሀሳባቸውን በጽሁፍ እና በንግግር እንዲገልፁ፣ በቋንቋው የሥዋሰው ህግና ቃላት ስርዓት መግባባት እንዲችሉ ለማድረግ እና የስነ ጽሁፍ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ነው። የትምህርቱ አቀራረብም ከቀላል ወደ ከባድ ፍሰት የተከተለ ሲሆን፤ በተማሪዎችመካከል ያለውን የትምህርት አቀባበል ልዩነት ግምት ውስጥ አስገብቷል። ትምህርቱንውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ ጽሁፎችና ስእሎች እንዲካተቱ ተደርጓል ። በተለያዩተግባራት ከተማሪዎች ነበራዊ ሁኔታ በመነሳት ቋንቋውን እንዲማሩ ለማድረግጥረት ተደርጓል።

በአጠቃላይ የተማሪው መጽሐፍ በሚዘጋጅበት ወቅት ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን መርሀ ትምህርትና የሚጠበቅ አጥጋቢ የመማር ብቃት ( MLC) መሰረት አድርጓል። በተጨማሪም ተማሪ ተኮርና አሳታፊ በሆነ ስነ ዘዴ ላይ በመመስረት ተማሪዎች በግልም ሆነ በጋራ እንዲሰሩና እንዲወያዩ የሚያደርጉ ተግባራት ተካተዋል።

# ምዕራፍ አንድ

## ሐገራዊ ባህል

የምዕራፉ አላማዎች

ከዚህ የምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ስለ አፈርሳታ ስርዓት ሂደት ትናገራላችሁ፡፡
- በንባብ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት ትርጉም ትለያለችሁ፡፡
- ውስብስብ ቃላትን አቀላጥፋችሁ ታነባላችሁ፡፡
- መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ አዳምጣችሁ ትፅፋላችሁ፡፡
- ከሰንጠረዥ ቃላት ትመሰርታላችሁ፡፡
- ለተለያዩ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ትጽፋላችሁ፡፡
- ለተለያዩ ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ታውቃላችሁ፡፡
- የምዕላድ ምንነትና አይነቶች ትረዳላችሁ፡፡
- በቃላት ስማዊ ሀረግ ትመሰርታለችሁ፡፡
- የልቦለድና ኢ-ልቦለድ ልዩነትን ታውቃላችሁ፡፡
- የፈሊጣዊ ንግግር ፍቺን ታውቃላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ ማዳመጥ

ተግባር

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. የምታውቋቸውን ተላለፊ በሽታዎች ተናገሩ፡፡
2. ስለምታውቋቸውን ተላላፊ በሽታዎች መተላለፊያና መከላከያ መንገዶች ተናገሩ፡፡
3. በአሁኑ ሰአት ለሀገር ስጋት የሆነው ተላላፊ በሽታ መተላለፊያና መከላከያ መንገዶች ይናገራሉ፡፡

**ሀ መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የጉበት በሽታ በሚል ርዕስ የቀረበውን ፅሁፍ ሲያነቡላችሁ በጥንቃቄ አዳምጡ፡፡ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ጥያቄዎችን በቃል መልሱ፡፡**

1. የጉበት በሽታ ምንድ ነው?
2. የጉበት በሽታ መተላለፊያ መንገዶችን ዘርዝሩ፡፡

3. የጉበት በሽታ ምልክቶችን ዘርዝሩ፡፡
4. የጉበት በሽታ መከላከያ መፍትሄዎች ምንድን ናቸው?
5. ስንት አይነት የጉበት በሽታዎች አሉ?

**ለ. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የጉበት በሽታ በሚል ርዕስ የቀረበውን ፅሁፍ ሲያንቡላችሁ ካዳመጣችሁ በኋላ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን ‹‹እውነት›› ስህተት የሆነውን ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት መልሱ፡፡**

1. በአሁኑ ወቅት የጉበት በሽታ መፍትሔ ያልተገኘለት ተላለፊ በሽታ ነው፡፡
2. የጉበት በሽታን በማምጣት የሚታወቀው ቫይረስ ሂፓታይተስ ቢ እና ሲ ነው፡፡
3. የጉበት በሽታን ለመከላከል የሚውሰዱ መፍትሄዎች አልኮል መጠጣት እና ሲጋራ ማጨስ ማቆም ነው፡፡
4. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሂፓታይተስ ሲ በሽታ ክትባት ተግኝቷል፡፡
5. የሄፓታይተስ ሲ በሽታ መኖሩ የሚታወቀው በደም ምርመራ ብቻ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት፡ መናገር


### ተግባር

**ሀ.መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት በቡድን ሆናችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡**

1. በአካባቢያችሁ ስለምታውቁት ባህላዊ የግጭት አፈታት በቡድን ክፍል ውስጥ ተወያዩበት፡፡
2. በአከባቢያችሁ ያሉትን ማህበራዊ ጉዳዮች ቤተሰባችሁን በመጠየቅ በክፍል ውስጥ ተናጋገሩበት፡፡ ለምስሌ ፡- እቁብ ፣እድር እና ሰርግ ስነ ስርአት ወዘተ.
3. ስለ አፈርሳታ ምንነትና ሂደት ታውቃላችሁ? ተነጋገሩበት፡፡

**ለ. የሚከተሉትን ምስሎች ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን ግለጹ፡፡**





## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

# አፍርሳታ

### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች፡፡

1. በአከባቢያችሁ የጠፋ ንብረት የሚመለስበት ማህበራዊ ልማድ አለ ? ሂደቱን ለክፍል ጓደኞችችሁ ተናገሩ ፡፡
2. አፈርሳታ ማለት ምን ማለት ነው?

ተበዳይ ማን በደል እንደፈጸመበት በውል በማያውቅበት ወቅት አንዱ ጎረቤቱ ላይ



ያለአግባብ ጣቱን ሊቀስር ይችላል፡፡ ለአብነት አንድ አርሶ አደር ከማሳው አምሽቶ ወደ ቤቱ በሚመጣበት ወቅት ለአይን ያዝ በሚያደርግ አካባቢ ሲደርስ ወንበዴዎች የያዘውን ንብረት ዘርፈውት ቢሰወሩ ማን እንዳጠቃው አያውቅም፡፡ በዚህም ምክንያት እገሌ ነው የዘረፈኝ ወይም ያዘረፈኝ እያለ ከብዙ ጎረቤቶቹ ጋር ግጭት ውስጥ ይገባል፡፡ በዚህ ጊዜ አፈረሳታ ይጠራና የቀዬው ህዝብ በሙሉ አንድ ጨላማ ስፍራ ላይ እንዲሰበሰብ ይደረጋል፡፡

ለአፍርሳታ የተሰበሰበው ነዋሪ ማን ያውቃል ስለጉዳዩ? እያለ ሲወያይ ከቆየ በኋላ ወንጀሉ ሲፈጸም እማኝ የነበረ ወይም ዘራፊዎቹ እነማን እንደሆኑ መረጃው ያለው ሰው ተመርጦ በህዝብ ፊት እንዲቆም ይደረጋል፡፡ በወቅቱም ዳኝነት ሊሰጥ የሚችል ሰው ይሰየምና ጉዳዩን ከእማኞች እንዲሰማ ይደረጋል፡፡ የዳኛው ስራ ሽምግልና ሲሆን “ነገርን ከስሩ ውሃን ከጥሩ” እንዲሉ እውነትን የመፈለጊያ ጥያቄ ከተሰብሳቢዎች ዘንድ ይቀበላሉ፡፡ ተበዳይም በጨለማ የተፈጸመበትን በደል በማስረዳት ወንጀለኞቹ እንዲጠየቁለት አቤቱታውን ያሰማል፡፡ እማኞቹም እነማን ዘረፋውን እንደፈጸሙ በማጋለጥ ለዳኛው ያስረዳል፡፡

በዚህ ወቅት ተጠርጣሪዎቹ በቦታው ከተገኙ ተነስተው ስለጉዳዩ እንዲያስረዱ ይጠየቃሉ፡፡ ነገር ግን በቦታው ከሌሉ በሌላ ቀን እንዲመጡ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ተሰብሳቢው ይበተናል፡፡ በድጋሚ በሚጠራ ጉባኤ ላይም ተጠርጣሪዎች ቀርበው የእምነት ክህደት ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ ዳኛውም ጉዳዩን ካዳመጠ በኋላ ፍርድ በመስጠት ግጭቱ እንዲበርድ ይደርጋል፡፡ ካስፈለገም ሁለቱም ወገኖች እንዲስማሙ

በዳይ ላይ የካሳ ክፍያ ይወሰንና ቤተሰቡም እርቀሰላም እንዲያወርድ አብሮ ማዕድ የሚቆርስበትን ቀን ቀጠሮ ይደርጋል፡፡

ተበዳይ የሚፈልገው ነገር እውነት ብቻ ነው፡፡ ይህንንም አቆምኩት፣ ገተርኩት፣ ረታሁት አሳመንኩት በሚል ቃል ይገልጽበታል፡፡ የሚፈለገው የሞራል አሸናፊነት ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ከሳሽም ዘራፊዎችም እርቅ በመፈፀም ኑሯቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ሀገር በቀሎቹ የግጭት አፈታት ስርዓቶች ግጭትን ከስሩ መፍታትና ከማድረቅ ባለፈ በየአካባቢው የሚከናወኑ በመሆኑ ለአርሶ አደሩ ጊዜ፣ ገንዘብ እና ጉልበት ቆጣቢ ናቸው፡፡

በተፈረደበት ሰው ላይ ቀላል የሆነ ቅጣት ስለሚጣል ህብረተሰቡን ለኢኮኖሚ ቀውስ አይዳረጉም፡፡ በግጭት አፈታቶቹ ላይ ዋናው የሚፈለገው የሞራል አሸናፊነት በመሆኑ ይቅር ባይነት እና አብሮነት እንደገና ከመገንባት አኳያ ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ይሻላሉ፡፡

በመሆኑም ከመደበኛው የፍትህ ስርዓት ጋር እያጣጣሙ እንዲቀጥሉ ማድረግ ይገባል፡፡ ነገር ግን አፈርሳታ አሁን አሁን እየቀረ የመጣ የግጭት መፍቻ ስርዓት ቢሆንም ይህን ስርዓት ወደ ቀድሞ ለመመለስ ትኩረት ያስፈልጋል፡፡

(ምንጭ፡- ጌትነት ተሰፋማርያም ጡመራ ገፅ ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ)

### ሀ. ከላይ በቀረበው ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. አፈርሳታ ለማህበረሰብ ሰላምና ስምምነት ምን ሚና አለው?
2. በአፈርሳታ ስርዓት የዳኞች ሚና መሸምገል ነው?
3. ሀገር በቀል የግጭት አፈታት ስርዓቶች ለማህበረሰብ ምን ጥቅም ይሰጣሉ?
4. እማኞች ማለት ምን ማለት ነው?
5. አፈርሳታ በአሁኑ ጊዜ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?
6. አፈርሳታ ምን ጠቀሜታ አለው?

### ለ. ለሚከተሉት ቃላት በምንበቡ መሰረት አቻ ፍቺ ስጡ፡፡ለምሳሌ፦ ተበዳይ ---- ተጎጂ

1. ዳኛ
2. ሽምግልና
3. ጣት መቀሰር
4. አፈርሳታ
5. ሥርዓት

**ሐ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ተሰማሚውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. በምንባቡ መሰረት በውል **የሚያውቁበት** ማለት ምን ማለት ነው?
   ሀ. ግልፅ በሆነ ለ በአካል ያልተገኘ ሐ. ዘመድ ሆነ መ. ሁሉም
2. ግጭት ማለት ምን ማለት ነው?

   ሀ. አለመግባበት ለ. ስምምነት ሐ. ወዳጅነት መ. ጓደኝነት

3. በምንባቡ መሰረት **ሽማግሌ** ማለት ምን ማለት ነው?

   ሀ. ዘመድ ለ. ሽምግልና ሐ. ምስክር መ. አስታራቂ

4. የአርሶ አደሩን ጊዜ፣ገንዘብ እና ጉልበት ቆጣቢ ነው፡፡ የተባለው ምንድ ነው?
   ሀ. ግጭት ለ. አፈርሳታ ሐ. ሀገር በቀል መ. ሽምግልና
5. በምንባቡ መሰረት የዳኛው ስራ ምንድን ነው?
   ሀ. ማስታረቅ ለ.መመሰከረ ሐ. ትዕዛዝ መቀበል መ. ሁሉም

## አቀላጥፎ ማንበብ

መነጠል:- ማለት ውስብስብ ቃላትና ሀረጋትን በመነጣጠል የማንበብ ዘዴ ነው::

ማጣመር:- ማለት ተነጣጥሎ የቀረቡ ቃላትን በማጣመር ማንበብ ነው::

መነጠልም ሆነ ማጣመር ዓላማ ለማንበብ አስቻጋሪ የሆኑ ውስብስብ ቃላትና ሀረጋት በትክክል የማንበብ ስልት ነው፡፡

ሀ. በ- ል-ዋለ - በት --------ባልዋለበት

ለ. እየ- ተርገፈገፍ - ኩ -----እየተርገፈገፍኩ

ሐ. ደህንነት-ኣችው-ን --------ደህንነታቸውን

ተግባር

**መ. የሚከተሉትን ቃላትንና ሀረጋት በመነጠልና በማጠመር አንብቡ**

1. የ - ተ - ዝረከ - ረከ - ች - ው

2. የ-ተቋቋ - መ- ው
3. አዛውንት- ኦች- ም
4. የተ-ዘረ - ዘሩ-ትን
5. እየ-ተጓጓ - ዘ
6. መ-ተሳሰብ- አቸው-ን
7. አረፈዳ -ኣችሁ

## ክፍል አራት፡- መፃፍ

### ተግባር

ሀ.አፈርሳታ የሚለውን ንባብ አቀላጥፋችሁ ከነባበችሁ በኋላ ስለ አፈርሳታ የተረዳችሁትን ሀሳብ በራሳችሁ አባበል አሰጥራችሁ ፃፉ፡፡

ለ. አፈርሳታና ሽምግልና ያላቸውን አንድነትና ልዩነት በአንድ አንቀፅ በጽሁፍ አቅርቡ፡

ሐ. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ አንድ የተማረ ሰው መልስ በሚል ርዕስ የሚያነቡላችሁን ምንባብ እያዳመጣችሁ በቃል ጻፉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ተግባር

የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ፡- ማለት አንድን ቃል በሌላ ቃል ተክተው አቻ ትርጉም የሚሰጡ ቃላት ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

1. አሜኬላ-------------እሾኽ
2. መዘከር--------------ማስታወስ
3. ህጻጽ--------------- እንከን፣ ጉድለት

**ሀ. ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ቃላት ከላይ በቀረበው በምሳሌው መሰረት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡**

1. ጎዳና ________________
2. አውራ ________________
3. የዋህ ________________
4. ዘንግ ________________
5. አንጋፋ ________________
6. ፋይዳ ________________
7. አቀበት ________________
8. ጮሌ ________________

9. ምኞት ________________

10.ነጻነት ________________

**ለ. በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ከሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ቃላት መስርቱ፡፡**

ለምሳሌ፡- ሀ. አሰበ ለ. አጨደ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተ | አ | ለ | በ | ገ |
| ነ | ሸ | ጨ | ጀ | ቸ |
| ቀ | ደ | ረ | ወ | ጠ |
| ጸ | ኘ | ፈ | ከ | ሰ |

1------------------- 6-------------------

2------------------- 7-------------------

3------------------- 8-------------------

4------------------- 9-------------------

5. ------------------- 10 -------------------

**ሐ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት በምሳሌው መሰረት ተቃራኒ ፍቺያቸው ጻፉ፡፡**

ለምሳሌ፡- ህያው --- ሙት

1. ልደት
2. ማፌዝ
3. ሰማይ
4. ኅረምሳ
5. ዘመድ
6. ለጋስ
7. ስውር
8. አያሌ
9. ደስታ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋሰው

# ምዕላድ

ምዕላድ ትርጉም አዘል የሆነና አነስተኛ ወደ ሆነ ትርጉም አዘል ክፍሎች ሊሸነሽነ የማይችል የመጨረሻ ንዑስ አሀድ ነው፡፡ ለምሳሌ ቤት፣ ሰው፣ ላም፣ ወዘተ ሲሆኑ ያለምንም ቅጥያ ራሳቸውን ችለው ትርጉም የሚሰጡ ናቸው፡፡

1. ነፃ ምዕላድ ራሳቸውን ችለው መቆም የሚችሉ ቃላት ናቸው፡፡
   ለምሳሌ፡- ወር፣ ማር፣ ቤት ወዘተ.
2. ጥገኛ ምዕላድ ራሳቸውን ችለው የማይቆሙ ነገር ግን ሰዋስዋዊ ተግባር ያላቸው ቃላት ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- -ኡ -ኣት - ነት - ዎች -ኦች

| | |
|---|---|
| ሀ. ቤት -ኡ ቤቱ | ሐ. ሀገር - ኣት |
| ለ. ሰው - ዎች ሰዎች | መ. ነጻ -ነት |

**ሀ. በሚከተሉት ቃላት ላይ ጥገኛ ምዕላድ ጨምራችሁ ፃፉ፡፡**

1. ዳቦዎች
2. ተግባር
3. ምሳሌ
4. ቃል
5. እርሳስ
6. ቤት
7. ልብ
8. ልጅ
9. ክብር
10. ወጣት

ስማዊ ሀረግ ማለት ሆሄያት እና ቃላት በስርዓት ተቀናጅተው ሙሉ ሃሳብ የማያስተላልፍ መዋቅር ነው፡፡

ሀ. የሀርር ብርቱኳን

ለ. የበቆሎ ገንፎ

ሐ. ግማሽ ዳቦ

መ. የስንዴ ቆሎ

**ለ. ቀጥሎ በተሰጡት ቃላት ስማዊ ሀረግ መስርቱ።**

1. ቤት
2. ኳስ
3. በሬ
4. ብርቱኳን
5. ሻይ
6. በግ
7. ሜዳ
8. ደብተር
9. ሰው
10. ብር

**ሐ. ቀጥሎ ለቀረቡት ሃሳቦች በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት በማስተካከል ዓረፍተ ነገሮችን አሟሉ።**

1. መሐመድ ጎበዝ ተማሪ ______________ (ናቸው)
2. ኬና ስልኩን ____________ (ስርቆት)
3. ዝናሽ ወደ ትምህርት ቤት ___________ (መጡ)
4. ሲፈን እንደ አባቱ በንግግር __________ (ጉብዝና) ነው።
5. ____________ (እነሱ) በዚህ ሩብ ዓመት አንደኛ ለመውጣት አቅጃለሁ።

ክፍል ሰባት፡- ሥነ-ጽሑፍ

ሥነ-ፅሁፍ የሰው ልጆች ሃሳባቸውን፣ ፍቅራቸውን፣ ለሌሎች ሰዎች የሚያስተላልፉበት ዘዴ ነው።

## ልቦለድ እና ኢ-ልቦለድ

ልብ ወለድ ማለት ደራሲ በገሃዱ ዓለም ዕውነታ ላይ ተመስርቶ ከአእምሮ እያመነጨው በተባ አገላለፅ፤ ልብ አንጠልጣይ በሆነ መንገድ የሚገለፅ ነው። ለምሳሌ ግጥም፣ ልቦለድ፣ ድራማ ወዘተ. ናቸው።

ኢ-ልቦለድ በእውነተኛ ክስተት ላይ የተመሰረተ ታሪክ ነው። በሳይንስ የተደገፈና ሊረጋገጥ የሚችል ነው። ምሳሌ፡- ዜና፣ የህይወት ታሪክ፣ ዘገባ ወዘተ. ናቸው።

ተግባር

**ሀ. የሚከተሉትን ጹፎች ልቦለድ ወይም ኢ-ልቦለድ መሆናቸውን ለዩ፡፡**

1. የሕይወት ታሪክ
2. ደብዳቤ
3. የቀን ውሎ
4. ድራማ
5. ግጥም
6. ዘገባ

## ፈሊጣዊ አነጋገር

ፈሊጣዊ አነጋገር ማለት በቃላት ልዩ ልዩ ዘዴ የመጠቀም አንደኛው መንገድ ነው፤ እያንዳንዱ ቃል ከሌሎችቃላት ጋር በሚቀናጅበት ጊዜ ከነበረው ፍቺ የተለየ ፍቺ የሚሰጥበት ሁኔታ ነው፡፡

ለምሳሌ፡-

- ልበ ብርሃን-- ቶሎ የሚገባው
- ሆዱን ሰጠ-- ሚስጢሩን ተናገር
- ልብ ገዛ -- አስተዋይ ሆነ
- ልቡ ተነሳ-- ለመሄድ ተቸኮለ
- ሆድና ጀረባ-- የማይገነኙ

**ለ. ለሚከተሉት ፈሊጣዊ ንግግሮች ከተሰጡት አማራጮች ፍቺ ፈልጋችሁ በፅሁፍ መልሱ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ጨለም ሲል | ለ. ውሸታም | ሐ. ቻይ /ታጋሽ |
| ሠ. አጋዥ/ረዳት | ረ. ቆንጆ | ሰ. ተቸገረ |
| በ. የልጅነት ወቅት | ቀ አስተዋይ | መ. ጋመ<br>ሸ. ቶሎ የሚያኮርፍ |

1. ልበ ሰፊ ----------------------
2. መሽት ሲል ---------------------
3. መልከ መልካም ------------------
4. ምጣዱ ሰማ -------------------
5. ቀን ጣለው --------------------
6. ቀኝ እጅ ------------------
7. ቆርጦ ቀጥል --------------------
8. ሆደባሻ -------------------
9 . ልባም --------------------
10. ለጋ ዕድሜ --------------------

ማጠቃለያ

## ክለሳ ጥያቄዎች

### ሀ. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች ለይታችሁ አሳዩ፡፡

1. በውበታችን ____________________________
2. በቤትሽ ____________________________
3. ስለተማሪዎች____________________________
4. በክፍላችን____________________________
5. በተመራማሪው____________________________

### ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ፡፡

1. የምዕላድ አይነቶችን በመዘርዘር ምንነታችሁን አስረዱ፡፡ ከዚያም ምሳሌ ስጡ፡፡
2. ሀረጋት እንዴት ይመሰረታሉ በምሳሌ አስረዱ፡፡
3. በልቦለድና ኢ-ልቦለድ መካከል ያለውን ልዩነት አስረዱ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## አፅዋፍ

የምዕራፉ አላማዎች
ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ፡-

- መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ጽሁፍ አድምጣችሁ ትጽፋላችሁ፡፡
- በአረፍተ ነገር ውስጥ ለቃላት አገባባዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ቅጥያዎችን ከዋና ቃል ለይታችሁ ትጽፋላችሁ፡፡
- በተሰጣችሁ ቃላት የተለያዩ ትርጉም አዘል ዓረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡
- የተረት ተረት ሂደትና አቀራረብን ትናገራላችሁ፡፡
- እንቆቅልሽ አጨዋወት ሂደት ትናገራላችሁ፡፡
- ውጥን ምሳሌያዊ ንግግሮችን በተገቢው አባባል ታሟላላችሁ፡፡፡፡
- በክፍል ውስጥ የውይይት ስርዓት ጠብቃችሁ ታካሂዳላችሁ፡፡
- የሰዋሰው ስህተት ያለባቸውን አረፍተ ነገሮችን አስተካክከላችሁ ትፅፋላችሁ፡፡

### ክፍል አንድ ማዳመጥ

ተግባር

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ኢትዮጵያ ስንት ክልሎች አሏት? ዘርዝሩ
2. የኢትዮጵያ አየር ጸባይ ሁኔታ ምንድ ነው?
   ስለ ኢትዮጵያ ሀገራችን ስያሜ ምን ታውቃላችሁ?

**ሀ. በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጡ፡፡**

1. ኢትዮጵያ በጥንት ዘመን በውጪው ዓለም ምን በመባል ትጠራለች?

   ሀ. አቢሲንያ ለ. ኢትዮጵያ ሐ. አይቲዮጵያ መ. መልስ የለውም

2. ኢትዮጵያ የሚለው ስም በጥንታዊነት የሚታወቀው በየትኛው ሀገር ፀሃፊዎች ነው?

   ሀ. በእንግሊዝ ለ. ቻይና ሐ. ግሪክ መ. ኬንያ

3. የድንቅነሽ ዕድሜ ስንት ነው?

ሀ. 3.2 ሚሊዮን ለ. 4.2 ሚሊዮን ሐ. 8.2 ሚሊዮን መ. 6.2 ሚሊዮን

4. ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መገኛ መሆኗን የሚገልፀው የትኛው አንቀፅ ነው?

ሀ. ሶስተኛ ለ. አራተኛ ሐ. አምስተኛ መ. አንደኛ

5. በቀደምት ጊዜ የኢትዮጵያ ግዛት እስከ የት ነበር?

ሀ. ቻይና ለ. ሮም ሐ. ፋርስ መ. የመን

ክፍል ሁለት፡- መናገር

**ሀ. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት በቡድን ሆናችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች በጋራ ተወያዩበት፡፡**

1. የነገው መምህር 2. የተማሪዎች ትራፊክ 3. የጥናት ዘዴ

ለ. ስለአዲስ አበባ ከተማ (አመሰራረት፣ አየር ንብረት፣ ክፍለ ከተማ፣ ስያሜ) የምታውቁትን ከሰዎች ወይም ከቤተሰባችሁ ጠይቃችሁ በክፍል ውስጥ ተነጋገሩበት፡፡

ሐ. ሀገርን በተለያየ ሙያ ማገልገል ያለውን ጠቀሜታ ዘርዝሩ ፡፡

## ክፍል ሦስት ማንበብ

ተግባር

### የመስቀል ወፍ

ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች፡

1. ከዚህ ቀደም የምታውቁትን የአዕዋፍ ዝርያዎች ተናገሩ፡፡
2. ስለ አዕዋፍ አኗኗርና ባህርያት ተነጋገሩበት፡፡
3. አዕዋፋት እንዴት ይራባሉ?

በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የአዲስ ዓመት መግቢያ የመጀመሪያው ወር መስከረም ከሌሎች ወራት በተለየ መልኩ በተፈጥሮ ውበት ያሸበረቀ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ የመስከረም ወር የክረምቱ መገባደጃ በመሆኑ በዕፅዋት አበባዎች በተለይም የአደይ አበባ የሚያብብበት በመሆኑ ለአይን ማራኪ ወቅት ነው፡፡ ከአደይ አበባ ውበት በተጨማሪም የመስከረም ወርን ለየት ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ ከወትሮው ለየት ያሉ ለአይን የሚማርኩ የአዕዋፋት ዝርያዎች (የመስቀል ወፍ) የሚታዩበት መሆኑ

ነው፡፡ አንዳአንድ ተባዕታይ የወፍ ዝርያዎች የላባቸውን ቀለም በመቀየር ወይም የጅራታቸውን ላባ በማሳደግ ከወትሮው ለየት ብለው በዓመት አንዴ በመስከረም ወር ይታያሉ፡፡ እነኚህ የወፍ ዝርያዎች በተለምዶ የመስቀል ወፍ ተብለው ይጠራሉ፡፡

የመስቀል ወፍ መስከረምን ጠብቀው ከሌላ አካባቢ የሚመጡ ሳይሆኑ ዓመቱን ሙሉ በሚገኙበት ቦታ የሚኖሩ ናቸው፡፡ ነገር ግን በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ በዓመት አንዴ መስከረምን ጠብቀው እንደ ሚመጡ እንጂ ዓመቱን ሙሉ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደሚኖሩ ግንዛቤ የለም፡፡ ምክንያቱም የመስቀል ወፍ በበጋ ወቅት ቀላማቸው ፈዛዛ ሆኖ ከሴት ወፎች ጋር በአካልም ሆነ በቀለም ብዙም ሳይለዩ ተመሳስለው በመኖራቸውና በቀላሉ በአካባቢው መኖራቸውን ማስተዋል ባለመቻሉ ነው፡፡

ወፎች ቀለማቸውን የሚቀይሩት በመራቢያ ወቅታቸው እንደሆነ አብዛኛዎቹ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ የመስቀል ወፎች በሚራቡብት ወቅት ላባቸውን ቀስብቀስ በሙሉ በማርገፍና በሌላ ቀለም ላባ በመቀየር ወይም የጅራት ላባቸውን በማሳደግ አምረውና በአካል ግዙፍ መስለው በመታየት ተቃራኒ ፆታን ለመሳብ የሚያደርጉት ጥረት ነው፡፡ ይህ ሂደትም በዓመት አንዴ በመስከረም ወር ብቅ ብለው ከዚያ በኋላ የሚጠፉ አዲስ የወፍ ዝርያዎች ያስመስላቸዋል፡፡

የመስቀል ወፍ የሚለው ስያሜ ወፎቹ ለየት ብለው የሚከሰቱበት ወቅት ኢትዮጵያ በዓመት አንዴ ከምታከብረው የመስቀል በአል (ደመራ) ጋር የሚገጣጠም በመሆኑ የተሰጣቸው ስያሜ እንደሆነ ይታመናል፡፡ የመስቀል ወፍ አንድ ብቻ ሳትሆን በርከት ያሉ የወፍ ዝርያዎችን የሚያጠቃልል የወል ስም ነው፡፡ እነኝህ በቪዱይዴ እና ፕሎሴይዴ በተባሉ ሁለት ቤተሰቦች ውስጥ የሚመደቡ ዝርያዎች ናቸው፡፡

(የኢትዮጵያ ብዝኃ ሕይወት ኢንስቲትዩት የአማርኛ ድረ-ገፅ ኅዳር 4ቀን 2012 ዓ.ም

**ሀ. የመስቀል ወፍ በሚል ርዕስ የቀረበውን ፅሁፍ አንብባችሁ የቀረቡትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ ‹‹እውነት›› ትክክል ካልሆነ ደግሞ ‹‹ሃሰት›› በማለት መልሱ፡፡**

1. የመሰቀል ወፎች ቀለማችውን የሚቀያይሩበት በመራቢያቸው ወቅት ነው፡፡
2. የመሰቀል ወፍ የሚባሉት ሁሉም ወፎች ናቸው፡፡
3. የመሰቀል ወፍ በደረቅ ወቅት ቀለማቸው ፈዛዛ ነው፡፡
4. በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጣር የመጀመሪያ ወር ነሐሴ ነው፡፡
5. የመሰቀል ወፎች መሰከረም ጠብቀው ከሌላ አከባቢ የሚመጡ ናቸው፡፡

**ለ. በምንባቡ መሰረት ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

1. የመስቀል ወፍ ቀለማቸው ፈዛዛ የሚሆነው በየትኛው ወቅት ነው?
   ሀ. በክረምት   ለ. በበጋ   ሐ. በበልግ   መ. በፀደይ
2. ወንድ የመስቀል ወፍ ቀለሙን ቀይሮ ለየት ብሎ የሚታየው መች ነው?
   ሀ. ህዳር   ለ. የካቲት   ሐ መስከረም   መ. ሰኔ
3. ለአይን ማራኪ ወቅት ነው። የተሰመረበት ቃል ፍቺ ምንድን ነው?
   ሀ. ሰቢ   ለ. አስጠሊታ   ሐ. ትልቅ   መ. ድብቅ
4. በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጣር የአዲስ ዓመት መጀመሪያ ወር የቱ ነው?
   ሀ. መስከረም   ለ. ጥር   ሐ. ታህሳስ   መ. ግንቦት
5. በተፈጥሮ ውበት ያሸበረቀ ነው። የተሰመረበት ቃል ፍቺ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ያመረ   ለ. የተዋበ   ሐ. ቆንጆ   መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

## ክፍል አራት፡-መጻፍ

### ተግባር

**ሀ. ለሚከተሉት ሀሳቦች ማብራሪያ በመስጠት በፅሁፍ አቅርቡ።**

1. ስለ ግል ንጽህና አጠባበቅ አጭር የሆነ ማብራሪያ አቅርቡ።
2. የመሰቀል ወፍ የሚለውን ምንባብ ዋና ሃሳብ በመረዳት በራሳችሁ አባበል ጻፉ።

**ለ. ቀጥሎ በቀረበው ሀሳብ መነሻ በማድረግ ታሪኩን አጠናቃችሁ ፃፉ።**

ሁለት ጓደኛማቾች በጥናት ወቅት አልተግባቡም። ያለመግባባታቸው መንስኤ ደግሞ በጥናት ወቅት ሁለቱም የተረዱትን ነገር ብቻ እውነት አድርገው ይወስዳሉ። ሁለቱም ተማሪዎች ርዕሰ ጉዳዩን የተረዱበት መንገድ ይለያያል። እነዚህ ሁለት ተማሪዎችን እንዴት አድርገን እናስታርቅ?

**ሐ. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ ግመል በሚል ርዕስ የሚያነቡላችሁን ፅሁፍ እያዳመጣችሁ በቃል ፃፉ፡፡**

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

| ቃል |
|---|
| ቃል ትርጉም የሚሰጥ የሆሄ ስብስብ ነው፡፡ ለምሳሌ ቤት፣ ሰው፣ ወንበር፣ ጨለማ፣ ተራራ ወዘተ. ቃላት ናቸው፡፡ |

ተግባር

**ሀ. በ‹‹ሀ›› ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት ተቃራኒያቸውን በ‹‹ለ›› ረድፍ ከተዘረዘሩት ቃላት ጋር አዛምዱ፡**

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1. መነሻ | ሀ. ግርጌ |
| 2. ውጥን | ለ. ተፈጥሮ |
| 3. ራስጌ | ሐ. ተነሳ |
| 4. ሰው ሰራሽ | መ. ያለቀ |
| 5. ወደቀ | ሠ. መድረሻ |

**ለ. በዓረፍተ ነገር ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡**

ለምሳሌ፡- አያንቱ ስለበረዳት በሩን <u>ገጠመችው፡፡</u> ፍቺ፡- ዘጋችው፡፡

1. ከአካባቢው የሚወጣ ፈሳሽ በጉድጓድ ውስጥ <u>መጠራቀም</u> አለበት፡፡
2. ከኢንዱስትሪዎች የሚገኘው ተረፈ ምርት በተገቢው <u>ቦታ</u> መቀመጥ አለበት፡፡
3. መሬትን <u>ወደታች</u> ማረስ አፈርን ለጎርፍ አደጋ ያጋልጣል፡፡
4. የውሃ <u>ብክለት</u> እንዴት ይፈጠራል?
5. ውሃ ለኃይል <u>ማመንጫነት</u> ያገለግላል፡፡

**ሐ. በሰንጠረዥ ውስጥ የሚገኘውን የቃላት ጨዋታ ተገቢውን ፊደላት በማስገባት አሟሉ፡፡**

<u>ወደታች</u>

1. የባንዲራ ስም
2. በእኩለ ቀን የሚበላ
3. የቋንቋ ትምህርት
4. የዕውቀት እናት
5. በጥሬው የሚበላ አትክልት
6. የዱር ስንሰሳት
7. የሀገራችን መጠጥ

<u>ወደጎን</u>

1. የጦርነት ተቃራኒ ሰላም
2. ህልም ታየው
3. ከከተማ ወጣ ያለ አካባቢ
4. የብሩክ ተመሳሳይ
5. ከድንጋይ የተፈለፈለ ቤተ-ክርስቲያን
6. የሰው መግባቢያ
7. ሲበላ የሚጣፍጥ

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 ሥ | ሳ | 2 ም | | | 3 | | 4 መ |
| | | | | | | | |
| | | | 8 | 7 ጠ | | | |
| 9 ቅ | | | | | | | |
| | | | 5 | | 6 ሚ | | ት |
| 10 ሳ | | | ሳ | | | | |
| 12 | ር | | | | 11 ቋ | | |

**መ ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት አቻ የሆነ ፍቺ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡**

1. ሶፍዑመር <u>ዋሻ ጥንት</u> የነበረ ቅርስ ነው፡፡

ሀ. አሁን ለ. ድሮ ሐ. ከርሞ መ. ቅርብ ጊዜ

2. የፈተና <u>ታዛቢ</u> የሆነው መምህር ዛሬ መጣ፡፡

ሀ. ተሳታፊ ለ. ተጋባዥ ሐ. ተመልካች መ. አድማጭ

3. ሎሚው በእጁ ላይ ሟሸሸ፡፡

ሀ. አበጠ　ለ. ለዘዘ　ሐ. ለመለመ　መ. ሟሟ

4.የአያንቱን መሞት በጠዋት አረዳው፡፡

ሀ. ነገረው　ለ. አበሰረው　ሐ. አወቀ　መ. ደበቀው

5. ገበሬው ብዙ ምርት አገኘ፡፡

ሀ. ጭድ　ለ. ሳር　ሐ. እህል　መ. ግርድ

ክፍል ስድስት፡- ሰዋሰው

**ቅጥያ**

ቅጥያ ማለት ከቃል መጀመሪያ፣ መካከል፣ መጨረሻና በኋላ የሚገቡ ሲሆን የተለያዩ ተግባር አላቸው፡፡ ለምሳሌ ጾታን መግለጽ፣ ቁጥር መግለጽ ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ልጅ | ልጅቷ | -ቷ | ሴት ጾታ አመልካች |
| ቤት | ቤቶች | -ኦች | ብዙ ቤት ቁጥር አመልካች |

## ተግባር

**ሀ. በተሰጡት ቃላት ላይ ከፊት ወይም ከኋላ ቅጥያ በመጨመር በጽሁፍ መልሱ፡፡**

ምሳሌ፡-　ተማሪ - ዎች -- ተማሪዎች

ተራራ - ኣማ -- ተራራማ

1. ቤት ______ ______
2. መጽሐፍ ______ ______
3. ደብተር ______ ______
4. ቦርሳ ______ ______
5. እርሳስ ______ ______

**ለ. በሰንጠረዥ ውስጥ ያሉትን ቅጥያዎች በዋና ቃል ላይ ጨምራችሁ ፃፉ::**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ኣዊ | ነት | ኦች | አኛ | ኣማ |

ለምሳሌ ደግ -- ነት -- ደግነት

1. ኩራት ----------------------------
2. ዳገት ----------------------------
3. ሰው ----------------------------
4. ዘመን ----------------------------
5. ደብተር ---------------------------

## ዓረፍተ ነገር

ዓረፍተ ነገር ሙሉ ትርጉም የሚሰጥ የቃላት ወይም የሀረጋት ስብስብ ነው::

- አቲናፍ አንድ ሊትር ወተት ገዛች::
- አብደላ ሆስፒታል ሄዶ ወንድሙን ጠየቀ::
- ካሰች ዘሬ ጠዋት ወደ ሀገሯ ተመለሰች::

**ሐ. በሚከተሉት ቃላት ትርጉም አዘል ዓረፍተ ነገር መስርቱ::**

1. ደብተር ________________________________________
2. ሰኞ ________________________________________
3. አሳ ________________________________________
4. ፈረስ ________________________________________
5. ቆረጠ ________________________________________

## ክፍል ሰባት፡- ሥነ-ጽሑፍ

### ተረት ተረት

በአንድ ሀገር ውስጥ በአንድ ዘመን እየተባለ የሚነገር ሆኖ በአብዛኛው ስነ-ምግባርን ለማስተማር የሚያገለግል ነው፡፡ ተረት ተናጋሪ ተረት ተረት ብሎ ይጀምራል፡፡ አድማጩም የመሰረት ይላል፡፡ አድማጭ በየመካከሉ እሺ እያሉ ያደምጣል፡፡ በመጨረሻም ተናጋሪው ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ በማለት ያጠናቅቃል፡፡

በድሮ ጊዜ አንድ ጫካ ውስጥ ብቻውን የሚኖር ቀበሮ ነበር፡፡ ይህ ቀበሮ የሚበላዉ ነገር በማጣቱ በጣም ይርበው እና ግራ ቀኙን ሲመለከትም የሚበላ ነገር በአካባቢዉ ያጣል፡፡ ታድያ ድንገት ወደ ሰማይ ቀና ብሎ ሲመለከት አንድ አሞራ ያያል፡፡ ይህ አሞራም ትልቅ ስጋ በአፉ ይዞ ሲበር ያንን ስጋ መብላት አለብኝ ብሎ አሰበ፡፡

ከዛም "አያ አሞራ! አያ አሞራ" እያለ ሲጣራ አሞራው ግን ሰምቶ እንዳልሰማ ሆኖ ዝም አለ፡፡ አሁንም ቀበሮው "አሞራ! አሞራ ሆይ! ስፈልግህ ነበር እኮ!" ቢለውም አሞራው አሁንም መልስ አልሰጠውም፡፡ ቀበሮው መናገሩን በመቀጠል ዛሬ ምን እንደተከሰተ ታውቃለህ? ሁሉም እንስሳት ተሰባስበው፤ የተለያዩ እንስሳትን እና አዕዋፍትን በእጩነት ካቀረቡ በኂላ፤ ሁሉም የራሱን አስተያየት ሰጥቶ ሲያበቃ በመጨረሻ አንተን መርጠውሃል አለው፡፡

አንተም ቆንጆ እና በፍጥነትህ የፈለግኸው ቦታ ቶሎ መድረስ እንደምትችል ስለሚያውቁ ሁሉም ወደውሃል፡፡ አናትህ ላይ ያለው ‹‹ነጩ ፀጉርህ ለዘውድ ማረፊያ ተስማሚ ነው›› ብለዋል፡፡ ነገር ግን አንድ መሟላት ያለበት ነገር አለ፡፡ ያም ድምፅህ ቆንጆ መሆን አለበት፤ ስለዚህም ይህን ለማረጋገጥ እኔን ‹‹ቤቱ ሂደህ ድምፁን ሰምተህ ና›› ብለው ላኩኝ፡፡ "ይህንን ታላቅ ሹመት ከፈለግህ ምን አይነት ድምፅ እንዳለህ መስማት እፈልጋለሁ" አለ::

በዚህን ጊዜ ቁራዉ የእንስሳቱ ሁሉ ንጉስ ሁኖ እንደሚመረጥ ሲያስብ ደስታው ከልክ ያለፈ ሆነ፡፡ ለቀበሮ ምን አይነት ጣፋጭ ድምፅ እንዳለው ሊያሰማው ቆ፡ ቆ፡ ቆቅ፡ ቆቆ፡ ቆክ እያለ መጮህ ጀመረ፡፡ አፉን ከፍቶ መጮህ ሲጀምር በአፉ ይዞት የነበረው ትልቁ ስጋ ወደ መሬት ወደቀ፡፡ ቀበሮው በፍጥነት ስጋውን መንትፎ ሮጦ አመለጠው ይባላል፡፡ ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ፡፡

(ምንጭ ህዝባዊ ተረክ)

## ተግባር

**ሀ በምንባቡ መሰረት .ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ ።**

1. ስጋውን በአፉ የያዘው ማነው?
2. <<አንተ ቆንጆ ነህ>> የተባለው ለማን ነው ?
3. ስጋውን መንትፎ የሮጠው ማን ነው ?
4. ታላቅ ሹመት ይሰጥሃል ያለው ማነው ?
5. ከዚህ ተረት ተረት ምን ተማራችሁ ?

## ምሳሌያዊ አነጋገር

ምሳሌያዊ አነጋገር ከስነ-ቃል ዘርፎች ውስጥ አንዱ ሲሆን፤ በቃልም ሆነ በፅሁፍ የሚተላለፍ መልዕክትን ውበትና ለዛ ያላብሳል፤ ሀሳብን እጥር ምጥን ባለ መልኩ ለመግለፅ ያገለግላል፡፡ ለምሳሌ

1. አፍንጫ ሲመታ አይን ያለቅሳል፡፡
2. የውኃና የእናት መጥፎ የለውም፡፡
3. አጉል ብልሃት ያደረሳል ከሞት፡፡
4. ለተራብ ቂጣ ለተጠማ ዋንጫ፡፡

**ለ. ውጥን ምሳሌያዊ ንግግሮችን ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ መርጣችሁ አሟሉ፡፡**

ሀ.በአረም ይመልሱ፡፡

ለ.እያደር ይጠራል፡፡

ሐ. በርበሬ ተወደስ፡፡

መ.ጣፊያ አንድ አለ፡፡

ሠ. ዳዋ ተመታ፡፡

1. እውነትና ንጋት ____________________
2. ስጋ ቁጠር ቢሉት____________________
3. አይጥ በበላ ____________________
4. በጨው ደንደስ____________________
5. አለባብሰው ቢያርሱ ____________________

## ማጠቃለያ

## ክለሳ ጥያቄዎች

### ሀ. ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ፃፉ፡፡

1. ችልተኛ ______________________
2. ድርብ______________________
3. አንድነት______________________
4. ረሃብ______________________
5. ማግለል______________________

### ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ፡፡

1. የመስቀል ወፎች ምን አይነት ወፎች ናቸው? አብራሩ
2. የቅጥያ አይነቶችን ዘርዝሩ፡፡
3. አረፈተ ነገረ ማለት ምን ማለት ነው?
4. በአከባቢያቸው ተረት መቼና እንዴት ይነገራል? አብራሩ
5. ተባብሮ መስራትን የሚገልፁ ሶስት ምሳሌያዊ አነጋገርን ተነገሩ፡፡

### ሐ. የሚከተሉትን ቃላት  በመጠቀም ዓረፍተ ነገረ መስርቱባቸው፡፡

1.ጉልበት

2. ንፅህና

3.ተላላፊ

4. ወተት

5. ስነ ምግባር

# ምዕራፍ ሶስት

## ሕይወት ታሪክ

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ስለህይወት ታሪክ ምንነት እና አይነት ትናገራላችሁ፡፡
- የቀረበውን ምንባቡ አንብባችሁና አድምጣችሁ መልስ ትመልሳላችሁ፡፡
- ባለድርብ ድምፅ ሆሄያትን ተጠቅማችሁ ቃላት ትፅፋላችሁ፡፡
- በቃላት ላይ መድረሻ ቅጥያዎችን ጨምራችሁ ትጽፋላችሁ፡፡
- በክፍል ውስጥ ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡
- የእጽዋትን ስም ለይታችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- ለቃላት ተመሳሰይ ፍቺ ትፅፋላችሁ ፡፡
- የዓረፍተ ነገር አካለትን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- አያያዥ ቃላትን በዓረፍተ ነገር አስተካክላችሁ ትጽፋላችሁ፡፡
- ስለስነቃል ምንነት ትናገራላችሁ፡፡
- የአፈ ታሪክን ምንነት ትረዳለችሁ፡፡

### ክፍል አንድ ማዳመጥ

1. አርበኛ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የሀገር ፍቅር እንዴት መግለጽ ይቻላል?
3. ሀገራችንን እንዴት ማገልገል እንችላለን?
4. ሀገርን መውደድ በምን መንገድ ይገለጻል?
5. ከሰዎች ጋር በሰላም ያለምንም ችግር አብሮ ለመኖር ምን ማድረግ አለብን?

**ሀ. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ ደጅ አዝማች ገረሱ ዱኪ በሚል ርዕስ የቀረበውን ህይወት ታሪክ ሲያነቡላችሁ በጥንቃቄ አዳምጣችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሀሳቡ ትክክል ከሆነ ‹‹እውነት›› ስህተተ ከሆነ ‹‹ሀሰት›› በማለት መልሱ**

1 ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ የተወለዱት በጅማ ከተማ ነበር፡፡

2 የደጅ አዝማች ገረሱ ዱኪ እናት ወይዘሮ አያንቱ ኤሌሞ ይባላሉ፡፡

3 ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በጦርነቱ ከተሰውት ውስጥ አንዱ በየነ( አባ ሰብስብ) ይባላሉ ፡፡

4 ፋሽስት ጣሊያን ለሁለተኛ ጊዜ ሀገራችንን የወረረው በ1988 ዓ .ም ነበር፡፡

5 አርበኛ ደጃዝማች ገረሱ ዱኪን የሚዘክር ሙዚየም በወሊሶ ይገኛል፡፡

**ለ. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ**

1. የደጃዝማች ገረሱ ዱኪ ልጅ ስም ማን ይባላል ?

ሀ. መኮንን ገረሱ　　ለ. ተፈራ ገረሱ　　ሐ. ደበሌ ገረሱ　　መ . መኮንን ገረሱ

2. ደጅአዝማች ገረሱ ዱኪ ዘመናዊ ጦር የታጠቀውን ፋሽስት <u>እያስበረገጉ</u> ሲል የተሰመረበት ቃል ፍቺ ምንድን ነው?

ሀ) እያስፈራሩ　　ለ) እያስደነገጡ　　ሐ) እያሳደዱ　　መ) ሁሉም

3. የእኚህን አርበኛ ታሪክ <u>የሚዘክር</u> የተሰመረበት ቃል ፍች ምንድንነው ?

ሀ) የሚሰፍር　　ለ) የሚለካ　　ሐ) የሚያስታውስ　　መ) የሚያውቅ

4. <u>የሞት ሽርት</u> ውጊያ፡፡ የተሰመረበት ቃል ፍች ምንድን ነው ?

ሀ) ትንቅንቅ　　ለ) ውሳኔ　　ሐ) ፍርድ　　መ) ህልውና

5. የጀግናው አርበኛ ገረሱ ዱኪ ሌላ ስሙ ማን ይባላል ?

ሀ ) አባሳፎ　　ለ ) አባ ሰብስብ　　ሐ ) አባ ቦራ　　መ) አባ ጣሰው

## ክፍል ሁለት መናገር

ሀ. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት በቡድን በቡድን ሆናችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡

1. ቅኝ ግዛት　　　2. ባህላዊ መድኃኒት　　　3. አርበኛ

ለ. ስለ አርበኝነት ከሰዎች ወይም ከቤተሰባችሁ ጠይቃችሁ በክፍል ውስጥ ተነጋገሩበት፡፡

ሐ. በአከባቢያችሁ የምታውቁትን በጎ ተግባር ላይ የተሰማራ ሰው ታሪክ ቤተሳባችሁን በመጠየቅ ከክፍል ጓደኖቸችሁጋር ተወያዩበት፡፡

መ. ከተሰጣችሁ ርዕስ ጉዳዮች ውስጥ አንዱን መርጣችሁ አጭር ጭውውት በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

ሀ. የስራ ክብርነት   ለ. ወታደር   ሐ መምህርና ተማሪ

**ክፍል ሦስት፡- ማንበብ**

## የአለም ሎሬት ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ

### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች፡፡

1. ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ የሚባል ሰው ታሪክ ታውቃላችሁ? ተናገሩ?
2. ለእናንተ መልካም ምሳሌ የሚሆናችሁ ሰው ማን ነው?
3. እናንት ወደ ፊት በምን ሙያ ሀገራችሁን ማገልገል እንደምትፈልጉ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

የአለም ሎሬት ‹‹ፕሮፌሰር ገቢሳ›› በአለም መድረክ ስማቸውንና የሀገራቸውን ስም ያስጠሩ ፀኃፊ፣ አርታኢ፣ መምህር፣ አማካሪ እና ተመራማሪ ናቸው፡፡ ሎሬት ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ ከአዲስ አበባ ስልሳ ሁለት ኪሎሜትር በስተ ምእራብ እርቀት ላይ በምትገኘው ኦሎንኮሚ በ1950 ተወለዱ፡፡ የቄስ ትምህርታቸውን በአካባቢያቸው ሲከታተሉ ቆይተው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በአካባቢያቸው ስላልነበረ 20 ኪሎሜትር በእግራቸው ተጉዘው ተከታትለዋል፡፡

የአለም ሎሬት ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጅማ የግብርና ቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጅ የተከታተሉ ሲሆን የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በእፅዋት ሳይንስ ከሐረማያ ኮሌጅ በ1973 ዓ.ም ወስደዋል፡፡ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ1990 በእፅዋት ሳይንስ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን እንዲሁም በ1985 በእጽዋት ማዳቀል እና ዘረመል ኢንጂነሪንግ አሜሪካ ከሚገኘው ፓርዱዩ ዩኒቨርስቲ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን አግኝተዋል፡፡

ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ ከሁለት መቶ በላይ የጥናት ጽሁፎችን ለህትመት ያበቁ ሲሆን አራት መፅሐፎችን የአርትዖት ስራ ሰርተዋል፡፡ ላለፉት 28 አመታት በአሜሪካ በሚገኘው ፓርዱዩ ዩኒቨርስቲ ያገለገሉት የአለም ሎሬት ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ ዩኒቨርስቲው አሉኝ ከሚላቸው ተመራማሪዎችም አንዱ ናቸው፡፡ ዶክትሬታቸውን ከተመረቁ በኂላ ወደ ሱዳን በመሄድ ማሽላ ላይ ምርምራቸውን ቀጥለዋል፡፡ በምርምራቸውም ድርቅን መቋቋም የሚችል የማሽላ ዝርያ ለአለም ማህበረሰብ ማበርከት ችለዋል፡፡ በ150 እጥፍ ምርታማነትን የሚጨምር የማሽላ ዝርያን ለአለም አበርክተዋል፡፡ ድርቅን መቋቋም

የሚችል የማሽላ ዝርያ ላይ ባስገኙት ውጤት ከአምስት ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ አፍሪካዊያን የምግብ ዋስትንን ማረጋገጥ ችለዋል፡፡

ጥናታቸው በዚህ ሳያበቃ በአፍሪካ ምርታማነትን በ40 በመቶ የሚቀንሰው እስትራጋ የሚባለውን አረም መቋቋም የሚችል የተሸሻለ የማሽላ ዝርያን ኢትዮጵያን ጨምሮ ለ12 አፍሪካ ሃገሮች ማቅረብ ችለዋል፡፡

ለእነዚህ እና መሰል የምርምር ስራዎቻቸው ከ17 በላይ አለም አቀፍዊ ፣ ሀጉራዊ እና ሀገራዊ ሽልማቶችን አግኝተዋል፡፡ እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2002 ወርልድ ፉድ ኖብል ፐራይዚ የተሸለሙ ሁለተኛው አፍሪካዊ ለመሆን በቅተዋል፡፡ በአፍሪካ ናሽናሊቲ ሳይንስ ሂሮ ሽልማት ከተሸለሙ አፍሪካዊ ሰባት ተመራማሪዎችም አንዱ መሆን ችለዋል፡፡

ከሰባ በላይ አለም አቀፍ እና ሀገራዊ ተቋሞች በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች ላይ የሰሩት የአለም ሎሬት ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ የአለም ህዝብ ቁጥር በጨመረ ቁጥር የምግብ ፍላጎት እየጨመረ ይመጣል፡፡ ይህን ለመቋቋም ሳይንስ ፣ ቴክኖሎጂ እና የምርምር ፈጠራ ውጤቶች በመጨመር ይሄንን መቋቋም የግድ የሚል ነው ይላሉ፡፡ ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ በ2005 በፕሬዘዳንት ባራክ ኦባማ የአለም አቀፍ የምግብ እና ግብርና ልማት ቦርድ ውስጥ እንዲሁም ከ2007 ጀምሮ በዩናይትድ ኔሽን ሴክሬተሪ ጄነራል ባኪሞን የዩዔን የሳይንስ አማካሪ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

ምንጭ፡- ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ኢንስቲቲዩት ኢትዮጵያ መስከረም 13/2013ዓ.ም

### ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጄታ ምን ምን ሙያ አላቸው?
2. ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጄታ በአሁን ጊዜ በምን እና የት በመስራት ላይ ይገኛሉ?
3. ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጄታ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የት ተማሩ?
4. ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጄታ ስንት ሽልማቶችን አግኝተዋል?
5. ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጄታ ማሽላ ላይ ያደረጉት የጥናት ውጤት ምንድ ነው?
6. ከፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ የህይወት ታሪክ ምን ተማራችሁ(ተረዳችሁ)?

### ለ. ከላይ በቀረበው ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን ‹‹እውነት›› ስህተት የሆነውን ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1. የአለም ሎሬት ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ የትውልድ ስፍራ አዳማ ከተማ ነው፡፡
2. የፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጄታ የትውልድ ዘመን 1960 ዓ.ም ነው፡፡
3. የፕሮፌሰር ገቢሳ በጥናታቸው ያገኙት እስትራጋ የሚባለው አረምን አርባ በመቶ

የሚቀነስ ነው፡፡

4. ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ ሁለት መቶ በላይ የጥናት ጽሁፎችን ለህትመት አብቅተዋል፡፡
5. ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ ድርቅን መቋቋም የሚችል የማሽላ ዝርያ ለዓለም ማህበረሰብ አበረክተዋል፡፡

ሐ. በ ‹‹ሀ›› ስር የተዘረዘሩትን በ‹‹ለ›› ሥር ካሉት ፅንስ ሀሳቦች በምንባቡ መሰረት አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ከሀረማያ ኮሌጅ ድግሪያችሁን ወሰዱ | ሀ. 1950 ዓ.ም |
| 2. የማሽላ ዘር አግኝቷል | ለ.ኦሎንኮም |
| 3. የትውልድ ስፈራ | ሐ.1973 ዓ.ም |
| 4. የትውልድ ዘመን | መ.150 |
| 5. ሽልማቶች አግኝተዋል | ሠ.17 በላይ |

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

ገላጭ ድርሰት፡- ማለት የአንድን ነገር ምንነት፣ አመጣጥ፣ ባህርያት፣ አይነት፣ መጠን፣ ቅርጽ፣ አሰራር፣ ጠቀሜታ፣ ጉዳት ወዘተ.የሚያብራራ የድርሰት አይነት ነው፡፡

### ተግባር

ሀ. ሀገራችሁን በምን ሞያ ማገልገል ትፈልጋላችሁ፡፡ ፍላጎታችሁን በጽሁፍ ግለጹ፡፡

ለ. ስለት/ቤታችሁ አመሰራረት በገላጭ ድርሰት አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

### የህይወት ታሪክ

የህይወት ታሪክ አጻጻፍ ሁለት አይነት ነው፡፡ የህይወት ታሪክ ማለት አንድ ሰው ከተወለደበት ጊዜ አንስቶ እስከኖረበት /ሞተበት/ ቀን ድረስ የፈጸማቸውን ተግባራት ሁሉ ያካትታል፡፡

1. ግለ ታሪክ ፡- የራሳችንን ታሪክ እራሳችን ስንጽፍ ነው፡፡

2. የሕይወት ታሪክ የአንድ ግለሰብ የህይወት ታሪክ ሌላ ሰው ሲጽፍ ነው፡፡

ሐ. ከሚከተሉት ታዋቂ ሰዎች አንዱን መርጣችሁ የሕይወት ታሪካቸውን ፃፉ፡፡

1. ዶክተር አክሊሉ ለማ
2. አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ
3. አርቲስት አሊ ቢራ

## ክፍል አምስት ቃላት

### ድርብ ድምጽ ፊደላት

ድርብ ድምፅ ያላቸው ሆሄያት ድርብ ፊደላት ይባላሉ፡፡ ፊደላቱን ደጋግማችሁ በማንበብ ድምፃቸውን እና ቅርፃቸውን ለዩ፡፡ ኗ ኟ ኋ ዟ ጧ ዷ ኳ ኻ ጇ ጿ ጒ ወዘተ. ናቸው፡፡

ቃላት ሲመሰርቱ ደግሞ ፡- ሟርት፣ እሷ፣ ተፈጥሯዊ፣ ቋንቋ፣ ቧንቧ፣ እህቷ፣ አኗኗር፣ ብርትኳን፣ ደጇ፣ በኋላ፣ወስዷት ወዘተ. ናቸው፡፡

ተግባር

**ሀ. ቀጥለው በተሰጣችሁ ድርብ ፊደላት ቃላት መስርቱ፡፡**

1. ኋ ___________________
2. ሟ ___________________
3. ቋ ___________________
4. ቧ ___________________
5. ቷ ___________________
6. ቿ ___________________
7. ሿ ___________________
8. ሷ ___________________
9. ሯ___________________
10. ጯ_____________

መድረሻ ቅጥያ ከዋና ቃል መጨረሻ ላይ የሚመጡ ሆሄያት ናቸው፡፡

ኦች ነት አማ አዊ ው

**ለ. በሚከተሉት ቃላት ላይ ስለ መድረሻ ቅጥያ ጨምራችሁ ፃፉ፡፡**

1. ፍየል
2. ሙሽራ
3. ህጻን
4. ልጅ
5. ሰው

## ሐ. የሚከተሉትን ስምና ምስል አዛምዱ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | ሬት | ሀ |  |
| 2 | ዋንዛ | ለ |  |
| 3 | ብሳና | ሐ |  |
| 4 | ጌሾ | መ |  |
| 5 | ጤናአዳም | ሰ |  |
| 6 | ዳማከሴ | ረ |  |
| 7 | ጽድ | ሠ |  |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 8 | ዋርካ | ሸ |  |
| 9 | ግራር | ቀ |  |

## ክፍል አምስት፡- ሰዋሰው

### የዓረፍተ ነገር አካላት

1. ባለቤት፡-ማለት በዓረፍተ ነገር ውስጥ ድርጊት የፈጸመውን አካል የሚያመለክት ነው፡፡

   ለምሳሌ፡- ጫሉማ በሬውን ጠመደው፡፡

2. ተሳቢ፡- ድርጊቱ የተፈፀመበትን የሚገልጽ ነው፡፡ ተሳቢን ለማወቅ ‹‹ማንን›› ወይም ‹‹ምንን›› በማለት መጠየቅ ይጠበቅብናል፡፡ ለምሳሌ፡- ጫሉማ በሬውን ጠመደው፡፡
   ምንን --- በሬውን

3. ግስ (መሰሪያ አንቀፅ)፡- የዓረፍተ ነገሩን ባለቤት እና ድርጊት የሚገለፅ ነው፡፡
   ለምሳሌ፡- ገመዳ በሬውን ጠመደው፡፡

**ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት ቃላት ትርጉም ያላቸው አረፍተ ነገሮች መስርቱ፡፡**

ለምሳሌ ሽልማት ታታሪ ተማሪዎች ሁልጊዜ ሽልማት ይገባቸዋል፡፡

1. ወተት ________________________________
2. ስንዴ ________________________________
3. ሱቅ ________________________________
4. መንገድ ________________________________
5. መኪና ________________________________
6. ልብስ ________________________________
7. ወርቅ ________________________________
8. አስቴር________________________________

**ለ. ተዘበራርቀው የቀረቡትን ቃላት አስተካክላችሁ ትክክለኛ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

ለምሳሌ፡- ሄደ፣ ቦረና፣ ዳዊት፣ ወደ፡፡

ሲስተካከል ዳዊት ወደ ቦረና ሄደ፡፡

1. ቁልፍ፣ ትምህርት፣ ነው፣ የዕድገት፣ መማር

   ____________________

2. ውሻ፣ አንድ፣ አለን፣ ድመት፣ ሁለት፣ እኛ፣ እና

   ____________________

3. መላ ፣ ስፖርት፣ የሚያንቀሳቀስ፣ ውኃ፣ ነው፣ ዋና፣ ሰውነትን

   ____________________

4. ደርቤ፣ ይወዳል፣ ኳስ፣ በጣም፣ መጫወት፣ እግር

   ____________________

5. ይወዳል፣ የታሪክ ፣ ልጁ ፣ ማንበብ ፣ መጻህፍትን

   ____________________

**ሐ. ቀጥሎ የተሰጡትን ባዶ ቦታዎች በተገቢ አያያዥች እና መስተዋድዶች አሟሉ፡፡**

1. ቶላ ትላንት---------------ጅማ መጣ፡፡ (ለ፣ከ)
2. በሻዱ ---------ገቢያ በግ ገዛች ፡፡ (ከ፣ ወደ)
3. ወንድሜ ዛሬ --------- አዳማ ይሄዳል፡፡(ስለ፤ወደ)
4. እኛ ተማሪዎች ---- ወታደር ሁልጊዜ ዝግጁ ነን፡፡ (እንደ፣ ቢሆንም)
5. እኔ ወደ አያቴ ቤት ከወንድሜ ------ በታክሲ ሄደኩ፡፡ (ስለ፤ጋር)

**መ. ከቀረቡት ሐረጋት መካከል ለእያንዳንዱ ባዶ ቦታ ተስማሚ የሆነውን መልስ መርጣችሁ ጻፉ፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ነጭ ልብስ | ከእህቴ ጋር | ሰፊ ገደል | ትልቁ ቤት |
| የተኛችው ድመት | የቋንቋ ትምህርት | የእጅ ዕሁፍ | |

1. ገመኔ የለበሰችው ________________ ያምራል፡፡
2. አልጋው ላይ ____________________ የአይጥ ድምፅ ሰምታ ነቃች፡፡
3. ፈተና ስለነበረብኝ ____________ሳጠና ነበርኩ፡፡
4. ሣሩ እየተመዘዘ ስላለቀ____________ አፈሰሰ፡፡
5. ከትምህርት ቤታችን ጀርባ____________ አለ፡፡
6. ____________________ ለሁሉም ትምህርት አይነቶች መሰረት ነው፡፡
7. ንባብና _______________ጎን ለጎን የሚሄዱ ክህሎት ናቸው፡፡

ክፍል ሰባት፡- ስነ ጽሑፍ

## ስነ-ቃል

ስነ-ቃል የአንድን ማህበረሰብ ታሪክ፣ ወግ እና ልማድ ከትውለድ ወደ ትውለድ በቃል የሚያስተላልፍ ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ አፈ ታሪክ ነው፡፡

አፈ ታሪክ፡- በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን አፈታሪክ እውነት ተብሎ የሚታመኑ ነገሮችን ስያሜ አሰጣጥ በምክንያት እያስደገፈ የሚገልፅ ነው፡፡

1. ዶሮ ማነቂያ፡ - ወንጀለኞች በስቅላት ይቀጡበት የነበረ ቦታ በጊዜ ብዛት ቦታው ላይ የስቅላት ቅጣት መፈጸም ቀረ፡፡ ሰዎችም ሰፈሩን ደሮ ማነቂያ እያሉ ይጠሩት ነበር፡፡ በጊዜ ሂደት ዶሮ ማነቂያ የሚል ቋሚ መጠሪያ ሆነ፡፡

2. አራት ኪሎ፡ - አራት መንገዶች የሚገናኙበት ቦታ ስለነበረ ነው፡፡

3. ሸጎሌ፡- ሼህ ኦጀሌ የቤንሻንጉል ጉምዝ አካባቢን ያስተዳድሩ የነበሩ የበርታ ብሄረሰብ ተወላጅ ነበሩ፡፡ እኚህ ሰው ከአጼ ምንሊክ ጀምሮ ለማዕከላዊው መንግስት ታማኝ ሆነው አካባቢውን ከጠላት ወረራ ሲከላከሉ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ሸጎሌ ቤተ መንግስት ነበራቸው፡፡ ሰፈሩ በስማቸው ሼህ ኦጀሌ ተባለ፡፡ በጊዜ ሂደት ሸጎሌ ተባለ፡፡

**ሀ. ለሚከተሉት የአዲስ አበባ ሰፈሮች ስያሜ ቤተሰቦቻቸሁን በመጠየቅ ክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡**

1. ስድስት ኪሎ
2. መርካቶ
3. አዲስ አበባ
4. ሽሮ ሜዳ
5. ፒያሳ

**ለ.የሚከተሉት ውጥን ምሳሌያዊ ንግግሮች በተገቢው አባባል አሟሉ፡፡**

1.የፉክክር ቤት ----------------
1. የቆጡን አውረድ ብላ --------------
2. የቀበጡ እለት -----------------------
3. ሲሮጡ የታጠቁት -----------------
4. አባይን ያላየ----------------------------

| ምንጭ ያመሰግናል፡፡ |
| --- |
| ሞት አይገኝም፡፡ |
| የብብቷን ጣለች፡፡ |
| ሳይዘጋ ያድራል፡፡ |
| ሲሮጡ ይፈታል፡፡ |

ማጠቃለያ
ክለሳ ጥያቄዎች

## ሀ. ከዚህ በታች በቀረቡት ቃላት ላይ ቅጥያዎችን ጨምራችሁ ፃፉ፡፡

1. ቃል ________________
2. ሮጠ ________________
3. ልብስ ________________
4. ደብተር ________________
5. ነጋዴ ________________

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትክክል መልስ፡፡**

1. ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ የሕይወት ታሪክ በአጭሩ ግለጹ፡፡
2. ባለ ድርብ ድምፅ ሆሄያት በመጠቀም ሶስት ቃላት መስርቱ፡፡
3. ስነ-ቃል በማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ፋይዳ ግለፁ፡፡
4. የሰፈራችሁ መጠሪያ ስያሜ እንዴት ተሰየመ?

# ምዕራፍ አራት

## አየር ንብረት

የምዕራፉ አላማዎች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- መምህራችሁ ሻይ የሚለውን ምንባብ ሲያነቡላችሁ አድምጣችሁ በቃል ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፡
- የአየር ንብረት የሚለውን ምንባብ አንብባችሁ ጥያቄዎቹን ትመልሳላችሁ፡፡
- በርዕሱ መሰረት ውይይት ክፍል ውስጥ ታደርጋላችሁ፡፡
- የነገሮች አሰራር ቅደም ተከተል ትናገራላችሁ፡፡
- ከሰንጠረዥ ውስጥ ቃላት ትመስርታላችሁ፡፡
- ለቃላት ተቃራኒ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- በተሰጣችሁ ርዕስ መሰረት አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡
- የዓረፍተ ነገሮችን አይነት ትለያላችሁ፡፡
- በዓረፍተ ነገር ውስጥ ተገቢ አያያዥ ቃላትን ታስገባላችሁ፡፡
- የስም አይነቶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የእንቆቅልሽ ምንነት ትረዳላችሁ፤ትጠያያቃላችሁ፡፡
- ለፈሊጣዊ ቃላት አቻ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡

### ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

#### ቅደመ ማዳመጥ ጥያቄ

1. የሻይ አፈላልን ሂደት በቅደም ተከተል ተናገሩ፡፡
2. ሻይ ለጤና ምን ጠቀሜታ አለው?
3. ስንት አይነት ሻይ ታውቃላችሁ?
4. ሻይ ለማፍላት ምን ምን ነገሮች ያስፈልጋሉ?

**ሀ. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ ሻይ በሚል ርዕስ የቀረበውን ፅሁፍ ሲያነቡላችሁ በጥንቃቄ አድምጡ፡፡ ከዚያም ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. የፖሊፌኖስ ተግባር ምንድን ነው?
2. የካፌን ጥቅም ምንድን ነው?
3. ሻይ ለጤና ምን ፋይዳ አለው?
4. የሻይ ቅጠል አይነቶችን ዘርዝሩ፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነውን ‹‹ አውነት›› ስህተት የሆነውን ‹‹ሀሰት›› በማለት መልሱ፡፡**

1. ሻይ የምግብ መፈጨትን ለማፋጠን ያግዛል፡፡
2. ቻይናውያን ሻይን አይጠቀሙም፡፡
3. ሻይ የተለጣጭ ጡንቻዎችን የግፊት ችሎታ ይቀንሳል፡፡
4. በሀገራችን አረንጓዴ ሻይ የተለመደ ነው፡፡
5. ሻይ በሰው ሰራሽ ዘዴ እንጂ በተፈጥሮ አይበቅልም፡፡

ክፍል ሁለት፡- መናገር

የአሰራር ቅደም ተከተል

የአንድ ድርጊት ወይም አፈፃፀም በጊዜ ቅደም ተከተል መግለፅ ነው፡፡

ለምሳሌ፡- የቡና አፈላል

- ከሰል ይያያዛል ወይም እስቶቭ ይለኮሳል፣
- ውኃ በማንቆርቆሪያ ይጣዳል፣
- ሲኒና ጀበና ታጥቦ ይቀርባል፣
- ቡናው ይታጠባል፣
- በብረት ምጣድ ወይም በማንከሽከሻ ቡናው ይቆላል፣
- በሙቀጫ ወይም በቡና መፍጫ ማሽን ይወቀጣል ወይም ይፈጫል፣
- የተወቀጠው ወይም የተፈጨው ቡና በጀበናው ይጨመርና የፈላው ውኃ ተጨምሮ ይጣዳል ፣
- ቡናው ከፈላ በኂላ ወርዶ እስኪሰክን ትንሽ ይቆያል፣
- ከዚያም በታጠበው ሲኒ ተቀድቶ ይጠጣል፡፡

1. **ከላይ በቀረበው ምሳሌ መሰረት ከዚህ በታች የተሰጡትን የነገሮች የአሰራር ቅደም ተከተል አንዱን መርጣችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡**

   1 የሽሮ ወጥ

   2 ቅንጨ

   3 ገንፎ

   4 እንጀራ

   5 ጨምቦ

2. ቤተሰባችሁ ወይም የህበረተሰብ መምህር ስለ አረንጓዴ አሻራ ምንነትና ዓላማ ጠይቃችሁ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተነጋገሩበት፡፡
3. መምህራችሁ በሚሰጣችሁ መመሪያ መሰረት በቡድን በቡድን ሆናችሁ ከሚከተሉት ጥያቄዎች በአንድ ላይ ከተወያያችሁ በኃላ፤ የደረሳችሁበትን ሃሳብ በቡድን መሪያችሁ አማካኝነት አቅርቡ፡፡

   ሀ. ጤና አጠባበቅ  ለ. የተመጣጠነ ምግብ  ሐ. የሻይ ጠቀሜታ

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

# አየር ንብረት

### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች፡-

1. በአካባቢያችሁ አንዳንድ ጊዜ የአየር ሁኔታ ሞቃት፤ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ቀዝቃዛ ይሆናል፡፡ ይህ ለምን የሆነ ይመስላችኃል?
2. ስለአየር ንበረት ምንነት ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተነጋገሩበት፡፡

የአየር ሁኔታ በቀን በሳምንት የተመዘገበ የሙቀት ዳመና፣ ዝናብ፣ የንፋስ፣ የቅዝቃዜ፣ ወዘተ.ሁኔታዎችን የሚገልጽ ነው፡፡ የአየር ንብረት በአንድ አካባቢ ለረጅም ጊዜ የተመዘገበ የሙቀት፣ የዝናብ መጠን፣ የአየር እርጥበት፣ የንፋስ ፍጥነት አማካይ ውጤት ነው፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ በረጅም ጊዜ የሚከሰት ነው ፡፡ሰፊ መልክዓ ምድራዊ ሽፋንም ያለው ነው፡፡ በቀናትና በወራት የሚቀያየር የንፋስ፣ የዝናብ፣ የሙቀትና፣ የቅዝቃዜ፣ ለውጥ ሲሆን ለውጡም የሚገለጸው በአነስተኛ መልክዓ ምድር ላይ ነው፡፡ ምክንያቶቹ ሙቀት አማቂ ጋዞች ከመጠን በላይ መከማቸታቸው ነው፡፡

የሙቀት አማቂ ጋዞችን ክምችት ያባባሰውና ለአየር ንብረት ለውጥ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገው የሰው ልጅ የድንጋይ ከሰልን፣ የተፈጥሮ ነዳጅና ጋዝን በሰፊው በመጠቀሙ ምክንያት ካርቦን ዳይኦክሳይድ የተሰኘውን ጋዝ ወደ አየር በመልቀቅ ቀድሞ የነበረውን የአካባቢ አየር ተፈጥሮአዊ ሁኔታ እንዲዛባ ምክንያት በመሆኑ የሰው ልጅ አሁን እየገጠመው ያለው ፈተና በሰው ሰራሽ ምክንያት በከባቢ አየር ውስጥ ባሉት የሙቀት አማቂ ጋዞች ለውጥ ሳቢያ፣ተፈጥሮም እንደ እሳተ ገሞራና ተፈጥሯዊ የሰደድ እሳትም በተከተለው አየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚደርሱ ናቸው ፡፡
የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸው ችግሮች የግብርና መሬት መቀነስ የሀገራችን አብዛኛው ህዝቧ የግብርና የሚተዳደር መሆኑ ይታወቃል፡፡ የህዝቧም ቁጥር በፍጥነት

እየጨመረ ይገኛል፡፡ የህዝብ ቁጥር መጨመር ተጨማሪ የምግብ አቅርቦትን የሚጠይቅ ነው፡፡ የምግብ ፍላጎትን ለማሟላት ሲባል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አካባቢ ላይ ተፅዕኖ ሲደርስ የግብርናው ዘርፍ ምርታማነት ሊቀንስና ቁጥሩ እያደገ የሚገኘውን ህዝብም መመገብ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

የመሬት መከላት /የአፈር መሸርሸር የኢትዮጵያ መልክዓ - ምድራዊ ተራራ ኮረብታማ እንዲሁም ዝቅተኛ ቦታዎችና ሜዳዎች የሚበዛበት ነው፡፡ ታላላቅ ወንዞችና ጅረቶች መነሻቸው ከደጋማው አካባቢ ነው፡፡ የመሬት አቀማመጥ ከወንዞች የፍሰት አቅጣጫ ጋር ተዳምሮ ለአፈር መከላት የተመቸ አድርጎታል፡፡አፈሯ እየታጠበ ወደ ጎረቤት ሃገር መጓጓዙ የተለመደ ሆኗል፡፡ ለአፈር መከላት ዋናው ምክንያት የወራጅ ውሃ እና በደረቅ ወቅትና በሞቃታማው አካባቢ የሚከሰተለው አውሎ ንፋስ ነው፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ የሚፈጥረው የጤናችግር በሰው ዘር ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡ እንደ ሰው ልጅ ሁሉ የቤትና የዱር እንስሳትም የችግር ተጠቂዎች ናቸው፡፡ በቆላማውና በበረሃማው የአገራችን ክፍል ተወስነው የነበሩት በሽታዎች ወደ ደጋው በመሸጋገር ችግር በመፍጠር ላይ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ወባና የጋንዲ በሽታ ተጠቃሽ ናቸው ፡፡

የአየር ንብረት ለውጡ ሲባባሰ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች ይቀንሳሉ፤ ከዘርፉ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬም ሆነ የሃገር ውስጥ ፍጆታ አቅርቦት አናሳ ይሆናል፡፡ የገፀ- ምድርና የከርሰ ምድር ውሃ መጠን መቀነስ፡፡ ዓለማችን ከ75% በላይ የሚሆነው መሬት በውሃ የተሸፈነ ነው፡፡ በአጠቃላይ የአየር ንብረት ለውጥ በሃገር የኢኮኖሚ ግንባታ ላይ ጉልህ የሆነ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡ ማህበራዊ ችግሮችን በማባባስ አለመረጋጋትን፣ ስደትን፣ ረሃብና ጦርነትን የመሳሰሉትን ሁነቶች ሊያባብሳቸው ይችላል፡፡

ምንጭ፡- የአብክመ የአካባቢ፣ የደንና የዱር እንሰሳት ጥበቃና ልማት ባለስልጣን የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት መጋቢት 2013 ዓ.ም

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልስ ስጡ፡**

1. የአየር ንብረት ለውጥ እንዴት ይከሰታል?
2. ሰው ሰራሽ የአየር ንብረት ለውጥ እንዲከሰት ምክንያት የሆነው ምንድን ነው?
3. ተፈጥሯዊ የአየር ንብረት ለውጥ እንዲከሰት ምክንያት የሆነው ምንድን ነው?
4. የአየር ንብረት ለውጥ ችግሮችን ግለጹ?
5. የአፈር መሸርሸር ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

**ለ. በምንባቡ መሰረት ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. የደን መብዛት ለ. የግድቦች መኖር
   ሐ. ሙቀት አማቂ ጋዞች መ. የችግኝ መተከል
2. የሀገራችን አብዛኛው ህዝብ የሚተዳደረው በምንድን ነው?

   ሀ. በንግድ ለ. በግብርና ሐ. በኢንዱስትሪ መ በልመና
3. የአለማችን መሬት በውኃ የተሸፈነው ምን ያህል ነው
   ሀ 55 % ለ. 65% ሐ. 75 % መ. 85 %
4. የበለጸጉ ሀገራት ሲል ምን ማለት ነው?
   ሀ. ድሃ ሀገራት ለ. ያደጉ ሀገራት ሐ. ታዳጊ ሀገራት መ. ሁሉም
5. የአየር ሁኔታ ለውጥ ችግር የሚያስከትለው በማን ላይ ነው?

   ሀ. የሰው ልጅ ለ. የቤት እንስሳት ሐ. የዱር እንስሳት መ. ሁሉም

**ሐ. ከምንባቡ ለወጡ በ «ሀ» ስር ለተዘረዘሩት ቃላት በ «ለ» ስር ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳያይ ፍቺ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መከማቸት | ሀ. ተፈጥሯዊ ያልሆነ |
| 2. መንስኤ | ለ. ተፅዕኖ |
| 3. ጫና | ሐ. ዙር |
| 4. ሰው ሰራሽ | መ. ሰበብ |
| 5. ዑደት | ሠ. መጠራቀም |

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

ሀ. የአንድ ታዋቂ ሰው የሕይወት ታሪክ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

ለ. የራሳችሁን ግለ ታሪክ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ሐ. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

1. ቀስበቀስ ----------------------------------------------------------------
2. በርካታ ----------------------------------------------------------------
3. ዘላቂ ----------------------------------------------------------------
4. አስፈላጊ ----------------------------------------------------------------
5. ዘመድ ------------------------------------------------------------

**መ. ከሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች አንዱን በመውሰድ አንድ አንቀፅ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

1. ሰላም     2. የእረፍት ቀን     3. ጓደኞቼ

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

**ሀ. ከዚህ በታች ከቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ የፍራፍሬ ስሞችን ፈልጋችሁ ጻፉ፡፡**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አ | ና | ና | ስ | ቲ |
| ሎ | ሚ | ጎ | ን | ማ |
| ሃ | ባ | ብ | ሙ | ቲ |
| ፓ | ፓ | ያ | ዝ | ም |

1 ሃባብ 5-------------------

2------------------- 6-------------------

3------------------- 7-------------------

4-------------------

**ለ. በ "ሀ" ስር ለተዘረዘሩት ቃላት በ "ለ" ስር ከተዘረዘሩት ቦታ ተቃራኒያቸው አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ህልም | ሀ. ቁር |
| 2. ሃሩር | ለ. እውን |
| 3. ቸር | ሐ. መበተን |
| 4. መሰብሰብ | መ. ንፉግ |
| 5. መርዶ | ሠ. ብስራት |

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋሰው

### የዓረፍተ ነገር አይነቶች

1. ነጠላ ዓረፍተ ነገር፡- አንድ በለቤትና አንድ ግስ ብቻ የሚይዝ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡
   ለምሳሌ፡- ፍራኦል ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡

2. ውስብስብ ዓረፍተ ነገር፡- ከአንድ ባለቤት እና ከአንድ ማሰረያ አንቀፅ በላይ የሚያዝ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡
   ለምሳሌ፡- ልጁ ቁርሱን በልቶ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡
   በልቶ እና ሄደ --- ግሶች ናቸው፡፡

### ተግባር

**ሀ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ነጠላና ውስብስብ መሆናቸውን ለዩ፡፡**

1. አሰቴር አባቷ ስለመጡ ተቀበለቻቸው፡፡-------------
2. ልጁ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡ --------------------
3. ጫላ ታታሪ ሰራተኛ ነው፡፡ --------------------
4. ገበሬ ቡናውን ለቅሞ ሸጠ፡፡ -------------
5. አወል ወፍራም ሹራብ ገዛ፡፡ --------------

## አያያዥ ቃላት

አያያዥ ማለት፡- የተለያዩ ቃላትን፣ ሀረጋትን ወይም ዓረፍተ ነገሮችን የሚያያይዝ ነው፡፡ እነዚህም አብይና ንዑሳን ሀሳቦች በጊዜና በድርጊት ቅደምተከተል እንዲቀርቡ የሚያድረጉ ቃላት ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡-

| | | | |
|---|---|---|---|
| በዚህ መሰረት | ነገር ግን | በመጀመሪያ | ይሁንእጂ |
| ይሁን እንጂ | በዚህም | ቀጥሎ | ከዚህ ሌላ |

**ለ. ተገቢውን አያያዥ ቃላት መርጣችሁ ዓረፍተ ነገሮቹን አሟልታችሁ ፃፉ፡፡**

ቢሆንም ስለዚህ ከሆነ

ነገረ ግን ስለሆነ ግን

ለምሳሌ ፡- 1. ዘንድሮ አንደኛ እወጣለሁ፤ <u>ስለዚህ</u> እሸለማለሁ፡፡

1. ቀዝቃዛ አየር ከባድ ______________ ሞቃት አየር―――――ቀላል ነው፡፡
2. ውሃ ተንኖ የሚቀር _________ ውቅያኖስችና ወንዞች ይደርቁ ነበር፡፡፡
3. ትምህርቱን በሚገባ ተከታትሏል፣________ በፈተና ከፍተኛ ውጤት አግኝቷል፡፡
4. ዝናብ እየጣለ ______________ወደ ትምህርት ቤት መሄድ አለብኝ፡፡
5. ጥላሁን ሲናገር ሰምቼዋለሁ ____________ሀሳቡን አልተቀበልኩትም፡፡

**ሐ. የሚከተሉትን ሁለት የተለያዩ ግሶችን አንድ ላይ በማምጣት ውስብስብ ዓ.ነገሮችን መስርቱ ፡፡**

ለምሳሌ፡- ዳዊት ወደ ቤቱ ገባ፡፡
ዳዊት እንጀራ በላ፡፡
ዳዊት ወደ ቤቱ ገብቶ እንጀራ በላ፡

1. ቴዎድሮስ ደብተር ገዛ፡፡ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡
   ________________
2. ሂክማ ከትምህርት ቤት ወጣች፡፡ ልብሷን ቀየረች፡፡
   ________________
3. ለሊሴ ጥያቄ ጠየቀች፡፡ ፈተናዋን ሰራች፡፡
   ________________
4. አሚር ፈተናውን ጨረሰ፡፡ ወደ ቤቱ ገባ፡፡
   ________________
5. ሪሀና ምሳዋን በላች፡፡ ገበጣ ተጫወተች፡፡
   ________________

## ስም

1. ስም ፡-ከቃል ክፍሎች አንዱ ሆኖ የሰዎች፣ የነገሮች መጠሪያ፣ መለያ ነው፡፡
   የስም አይነቶች

1. የተጸውዖ ስም፡- አንድን ሰው ወይም ነገር ከሌሎች ለይተን የምንጠራበት መለያ ነው፡፡ ምሳሌ፡- ሱራፌል፣ ዳውድ፣ ደቻሳ ወዘተ.
2. የወል ስም፡- የተመሳሳይ ባህርይ፣ መኖሪያ፣ አፈጣጠር፣ ያላቸው ነገሮች በጋራ የምንጠራበት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ተማሪ፣ ቤት፣ መኪና፣ ሰው፣ ወዘተ.
3. የረቂቅ ስም፡- ሊጨበጡ፣ ሊዳሰሱ፣ የማይችሉ ስሞች መጠሪያ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- እውቀት፣ ሰላም፣ ደስታ፣ ክፋት፣ ደግነት፣ ወዘተ.
4. የጥቅል ስም፡- የብዙ ነገሮች የጋራ መጠሪያ ነው፤በአንድ ላይ ቢጠሩም በውስጣቸው ሰፊ ልዩነቶች አላቸው፡፡ ለምሳሌ፡- አልባሳት፣ ፍራፍሬ፣ አትክልት፣ አራዊት ወዘተ.

**መ. የሚከተሉትን ስሞች የወል፣ የረቂቅ፣ የጥቅልና የተፀውዖ የሆኑትን ለዩ።**

1. ዲሪባ ---------------------------------
2. ቦንቱ ---------------------------------
3. አስተማሪ ---------------------------------
4. ፖሊስ ---------------------------------
5. አትክልት ---------------------------------
6. እንስሳ ---------------------------------
7. ጅብ ---------------------------------
8. ላም ---------------------------------
9. ብርሃን -----------------------------
10. ሰላም ------------------------------

**ሠ. ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላት በተገቢው ቦታቸው በማስገባት ዓረፍተ ነገሮቹን አሟሉ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ተመረቀች | ነሐሴ | ሄደ | ጀሚላ |
| ዶክተር | ቅዳሜ | ይዘንባል | ተመለሰች |
| ተመረምራለች | | | |

1. በ ____________________ ወር ዝናብ ________________።
2. ________________ ትናንትና ከአምቦ በመኪና መጣች።
3. ኢዮብ በሩጫ ወደ ቤቱ __________________።
4. የወይዘሮ ሲፈን ልጅ ____________________ ዕለት __________።
5. ______ ነቢያት በሽተኞቿን በጥንቃቄ _____ ።

ክፍል ሰባት፡- ሥነ-ጽሁፍ

# እንቆቅልሽ

በተምሳሌታዊ ስልት ሆኖ በጥያቄ መልክ የሚቀረብ ሲሆን፣ ጥያቄውን በጥሞና በማስተዋል ትክክለኛውን መልስ ወይም ፍቺ ለማግኘት አእምሮን በሚገባ የሚያሰራ ነው፡፡ የሰው፣ የእንስሳትና የተፈጥሮ ልዩ ልዩ ባህርይና ቅርፅ እንዲገነዘቡ የሚያደረግ የውድድር መንፈስ የሚታይበት የጥያቄና መልስ ሂደት ነው፡፡

ተግበር

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት የእንቆቅልሽ ጥያቄዎች ከሳጥን ውስጥ በመምርጥ መልሶች ስጡ፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጨለማ | ፈንዲሻ | በር | ነፍሰጡር |
| ጃርት | ምጣድ | ዶሮ | ውሻ |

1. ነጭ በሬ ጥቁሩን በሬ ቀስቅሶ ተኛበት ----------------- ሸበት
2. እህልና ሰው በአንድ ስልቻ ተቋጥረው ------------------------------
3. ሲቀመጥ ረጅም ሲቆም አጭር ------------------------------------
4. ውኃ ጠጥታ የማትሸና ----------------------------------------
5. ሲመሸ ወደውጭ ሲነጋ ወደቤት -----------------------------------
6. ነጭ ተቀብሎ ቀይ የሚሰጥ ----------------------------------------
7. ቀይ ቅል ዛፍ ላይ ትሰቀል -------------------------------------------
8. ጥቁር ፈረስ ቼ ቢሉት አይመለስ -------------------------------------
9. ጦሯ መቶ ሃምሳ ስትሄድ ምድር ዳብሳ ------------------------------

**ለ. ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገር ከሳጥን ውስጥ ፍቺ መርጣችሁ ጻፉ፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| 1ተሳካለት | 2. ቀዥቃዣ | 3. ትልቅ ድስት |
| 4.በብዛት | 5. ፍርሀት ፍርሀት አለው | |
| 6.ሚስጢሩን ገለፀ | 7. ዛተ፣ፎከረ | |

1. በገፍ ---------------------------
2. በለስ ቀናው -----------------------------
3. ባርባር አለው ------------------------------
4. ቆሌ ቢስ ------------------------------
5. በገፈጅ ------------------------------
6. ቡራ ከረዩ አለ ------------------------------
7. ሆዱን ሰጠ ------------------------------

ማጠቃለያ

ክለሳ ጥያቄዎች

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትክክል መልሱ፡፡**

1. የአየር ንብረት ለውጥ እንዴት ይከሰታል?
2. አያያዥ ቃላት በመጠቀም ሁለት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡
3. የስም አይነቶችን ዘርዝሩ::
4. የእንቆቅልሽ ጫዋታ ሂደትን አስረዱ፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡**

1. በላ------------------------------
2. ወሰደ---------------------------
3. ቸረ----------------------------
4. ብዙ----------------------------
5. ኃይል--------------------------

**ሐ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጡ፡፡**

1. ከሚከተሉት አንዱ የወል ስም ነው፡፡

ሀ. ከበደ ለ. ሐይቅ ሐ. ላም መ. ዶሮ

2. ከሚከተሉት አንዱ የተጸውዖ ስም ነው፡፡

ሀ. ፍራፍሬ ለ. አራዊት ሐ. አእዋፍ መ. ንብ

# ምዕራፍ አምስት

## ቅርስ ሀብት ነው

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- ቅርስ በሚል ርእስ የቀረበውን ምንባብ ታነባላችሁ
- የደብዳቤን ምንነት ትናገራላችሁ ፡፡
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ትፅፋላችሁ
- ቃላትን በማጥበቅና በማላላት ታነባላችሁ ፡፡
- የእንስሳት ስሞችን ታውቃላችሁ፡፡
- መጠይቃዊ ቃላትን በአረፍተ ነገር ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡
- የልጆች ጨዋታ ትጫወታላችሁ፡፡
- የግስ ቅርፆችን ትቀይራላችሁ፡፡

### ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

#### ቅደመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በምትኖሩበት አካባቢ የምታስተውሏቸው ምን ምን ነገሮች አሉ?
2. በአካባቢያችሁ ካሉ ነገሮች አደጋ የሚያስከትሉ እና አደጋ የማያስከትሉ ነገሮች ምን እንደሆኑ ዘርዝራችሁ ግለፁ፡፡
3. አካባቢያችንን ቀድመን ማወቅ ምን የሚሰጠን ጠቀሜታ ይኖራል?
4. አደጋ እና አካባቢ ምን ተያያዥነት አላቸው?
5. እናንተ አካባቢ ያሉ ልጆች ምን ዓይነት ጫወታዎችን ይጫወታሉ?

ሀ መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ ‹‹አካባቢን ማወቅ›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ፅሁፍ ሲያነቡላችሁ በጥንቃቄ አዳምጡ፡፡ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ስትክክል የሆነውን ‹‹እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት  በቃል መልሱ፡

1. በገጠርና በከተማ  የሚኖሩ ህፃናት የመጫወቻ ቦታቸው ተመሳሳይ ነው፡፡

2 .በገጠር አካባቢ አብዛኛውን ጊዜ  የአደጋ መንስኤ መኪና ነው፡፡

3.ህፃናት አካባቢያቸውን በደንብ እንዲያውቁ ማድረግ የወላጆች ግዴታ ነው፡፡

4. በከተማ በሚኖሩ ህፃናት ላይ አንዳንድ ግለሰቦች ጥቃት ሲያደርሱ ይስተዋላል፡፡

5 በመኪና መንገድ ላይ ኳስ የሚጫወቱ  ህፃናት ራሳቸውን ለአደጋ ያጋልጣሉ ፡፡

## ክፍል ሁለት መናገር

1. በአከባቢያችሁ በሚገኙት የቱሪስት መስህብ የሆኑ ቦታዎች በመሄድ የተመለከታችሁትን ጉዳይ በዝርዝር አስረዱ፡፡
2. በአዲስ አበባ የሚገኙትን ቅርሶች ዘርዝሩና የሚገኙበትን ቦታ ጥቀሱ፡፡
3. አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ ሀውልቶችን ስም እና ጠቀሜታ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተነጋገሩበት፡፡

## ክፍል ሦስት፡- ማንበብ

# ቅርስ

### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች፡፡

1. ቅርስ ምንድን ነው?
2. ቅርስ ለሀገር ምን ጠቀሜታ አለው?
3. በምትኖሩበት አካባቢ ምን አይነት ቅርሶች አሉ?
4. ቅርሶች በስንት ይከፈላሉ?



ቅርስ የአንድ ሀገር የታሪክና የባህል መረጃ ነው፡፡ ስለዚህም የቅርስ ክምችት የጥበብ ምንጭ በመሆኑ ከፍተኛ የሆነ ጥቅም አለው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የህብረተሰብን እድገት፣ የታሪክ ጉዞና ባህላዊ ሁኔታዎች ጠንቅቆ ለመረዳትና ለማወቅ የዕውቀት ምንጭ በመሆን ያገለግላል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የአሁኑ ትውልድ ካለፈው ጥበብ በመቅሰም ከዘመኑ ጥበብ ጋር በማገናዘብ የጥበብ ፈጠራ ችሎታውን እንዲያዳብር ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል፡፡ ብርቅና ተደናቂ የሆኑትን የሀገሪቱን

የታሪክ ቅርሶች ለመመልከት የሚጓጉትን የውጪ ጎብኚዎች በማሳብ በምጣኔ ሀብት እድገት በኩል የውጪ ምንዛሬ ያስገኛል፡፡ ከዚህም ሌላ ቅርስ ለከፍተኛ ምርምርና ጥናት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

ቅርስ በአሰራርና በጥበባዊ ይዘቱ የህብረተሰቡን የፈጠራ ችሎታ ለማዳበርና ከዘመናዊው የቴክኖሎጂ እውቀት ጋር በማዋሃድ አዳዲስ  ነገሮችን ለመፍጠር ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል፡፡

ይህንን የመሰለ ጥቅም የሚሰጡ የታሪክና የባህል ቅርሶች በሚገባ ተመዝግበው በጥንቃቄ መጠበቅና መያዝ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በአገራችን በአሰራርና በጥበባዊ ይዘታቸው ብርቅና ድንቅ የሆኑ ቅርሶች በየቦታው ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ ቀደም ሲል ለእነዚህ ቅርሶች ብዙም ጥበቃና እንክብካቤ ባለመደረጉ በርካታ የቅርስ ሀብት የመበላሸት፣ የመጥፋት፣ የመሰረቅና የመሸጥ እድል ገጥሟቸዋል፡፡ ቅርሶች በዚህ አይነት ጉዳት በደረሰባቸው ቁጥር የሰፊው ህዝብ መረጃዎች አብረው ይጠፋሉ፡፡ ሁኔታው በዚህ ከቀጠለም ስለኢትዮጵያ መረጃዎች አይኖሩም፡፡

ስለሆነም የታሪክና የባህል ቅርሶች በሚገባ እንዲጠበቁና እንዲያዙ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠቱ የሚመለከተው አካል የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ታሪካዊ ቅርሶች ተመዝግበው አስፈላጊው  ጥበቃና ቁጥጥር በመደረግ ላይ ነው፡፡

ቅርሶች ስለ አንድ አገር ታሪክ፣ ባህልና ማህበራዊ ኑሮ ከጥንት ቅርሶች በተጣራ ሁኔታ አስፈላጊው ምዝገባ እየተደረገ የተመዘገቡባቸው ቅጾች በተገቢው ቦታ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ምዝገባው ለቅርሶች ደህንነት እና እንክብካቤ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ በክልሎች ለሚገኙ ቅርሶችም አስፈላጊው ምዝገባ ከተደረገ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን ብሄራዊ ቅርሶች ለይቶ ለማወቅና ጉዳት እንዳይደርስባቸው በየጊዜው አስፈላጊውን ቁጥጥር ለማድረግ ብልሽት ከደረሰም በቀላሉ ለማደስና ለመጠገን እንዳይሸጡና እንዳይለወጡ ለመከላከል ከማስቻሉም ሌላ ቅርስ የአንድ ሀገር የታሪክና የባህል መለያ ጥበባዊ ውበቱና  በአሰራሩም ብሄራዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊነት ስላለው ህበረተሰቡ ሊንከባከበውና ሊጠብቀው ይገባል፡፡

ምንጭ፡- ጥር 26/2000 ዓ.ም በቅርስ ምዝገባና ቁጥጥር መምሪያ በተካሄደ ሲምፖዚየም የተዘጋጀ ተሻሽሎ የቀረበ፡፡

## ተግባር

**ሀ. በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምርጡ**

1. ለቅርሶች ምን አይነት አስፈላጊ ድርጊት ሊደረግ ይገባል?
   ሀ. እንክብካቤ   ለ. ቁጥጥር   ሐ. ጥበቃ   መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡
2. በምንባቡ መሰረት የታሪክና የባህል መረጃዎች የሚባሉት እነማን ናቸው?
   ሀ. ቅርሶች   ለ. ወጎች   ሐ. ልምዶች   መ. መረጃዎች
3. በምንባቡ ውስጥ ብርቅና ድንቅ ሲል ምን ማለቱ ነው?
   ሀ. ውብ   ለ. ተፈላጊ   ሐ. ውድ   መ. ሁሉም
4. እንደምንባቡ አገላለፅ የፈጠራ ችሎታ ምስክር የተባሉት ምኖች ናቸው?
   ሀ. ቱሪስት   ለ. የውጭ ምንዛሬ   ሐ. ቅርሶች   መ. ትውልዶች
5. ‹‹መንግስት ከፍተኛ ትኩረት እያደረገ ነው›› የተባለው በምን ላይ ነው?
   ሀ. ለቅርሶች   ለ. ለታሪካዊ ቦታዎች   ሐ. ለሀገር ሀብት   መ. ሁሉም

**ለ በ «ሀ» ስር የተዘረዘሩትን ቃላት በ «ለ» ስር ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳያቸውን አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ቅርስ | ሀ. ጠቃሚ |
| 2. አስፈላጊ | ለ. ቱሪስት |
| 3. ጎብኝ | ሐ. ብዙ |
| 4. በርካታ | መ. ሀብት |
| 5. ብሔራዊ | ሠ. ሀገር አቀፍ |

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

ደብዳቤ፡- መልእክትን ከአንድ ሰው ወደ ሌላው ሰው በአካል ለማናገኘው መልዕክትን በፅሁፍ ለማስተላለፍ የምንጠቀመው ዘዴ ነው፡፡


# የደብዳቤ ክፍሎች

ሀ.መግቢያ፡- ቀን፣ ወር፣ ዓ.ም እንዲሁም ሰላምታ ይፃፍበታል፡፡

ለ. ሐተታ፡- ሊተላለፍ የሚፈልገው ዋና መልዕክት በዝርዝር ይቀርብበታል፡፡

ሐ. መደምደሚያ፡- በሀተታ የቀረበው ዝርዝር ሀሳብ የሚጠቃለልበት መሰናበቻ ክፍል ነው፡፡

ለምሳሌ፡-




የዘመድ ደብዳቤ

ቀን ---------------
ፖ.ሣ.ቁ-----------

ለውድ አባቴ ለአቶ ዘላለም መንግስቱ፣ ለውድ እናቴ ወይዘሮ አያንቱ ቦንሳ፣ እንዲሁም ለቤተሰቡ በሙሉ፣ ለጤናችሁ እንደምን ከርማችኋል? እኔ ከእናንተ ናፍቆትንና ሀሳብ በስተቀር በጣም ደህና ነኝ፡፡

አባቴ ጤንነቴ በመልካም ሁኔታ ላይ ቢገኝም የገንዘብ ችግር ስላጋጠመኝ ትምህርቴን በሚገባ መከታተል አልቻልኩም፡፡ ባለፊው ወር ገንዘብ እንድትልኩልኝ በሰው በኩል ደብዳቤ ፅፌላችሁ ነበር፡፡ ነገር ግን ደብዳቤው ስላልደረሳችሁ ገንዘቡ አልደረሰኝም፡፡

በመጨረሻም በጣም ናፍቃችሁኛል፡፡ በአካል እስክምነገናኝ ድረስ ደህና ሁኑ፡፡

ለሊሴ ኩምሳ

ፊርማ

ሀ. ለጓደኛችሁ አንድ የሰላምታ ደብዳቤ ፃፉ፡፡

ለ. ከላይ በቀረበው ደብዳቤ መሰረት ለጓደኛችሁ ደብዳቤ ጻፉ፤ ከዚያም ተቀያይራችሁ የፊደል ስህተት አስተካክሉ፡፡

ሐ. ‹‹የልደት ቀኔ ›› በሚል ርዕስ ሁለት አንቀጽ ጻፉ፡፡ ከጻፋችሁ በኃላ የፊደልና የስርዓተ ነጥብ ስህተት እንዳይኖር ደግማችሁ በማንበብ አስተካክሉ፡፡

መ. ቅርስ የሚለውን ምንባቡ የመጀመሪያ አንቀፅ ዋና ሃሳብ በራሳችሁ አባባል በአጭሩ ፃፉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላትን ማጥበቅና ማላላት

### ተግባር

**ሀ. በሚከተሉት ቃላት ሁለት ትርጉም ያላቸውን ዓረፍተ ነገር ስሩ፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ለምሳሌ፡- | ልጁ ኳሱን ለጋ | ሲጠብቅ | መታ |
| | ልጁ ለጋ ነው፡፡ | ሲላላ | ሕጻን |

1. መላ ----------------------- -----------------------
2. ዋና ----------------------- -----------------------
3. በራ ----------------------- -----------------------
4. አዛባ ----------------------- -----------------------
5. ገና ----------------------- -----------------------
6. ቀና ----------------------- -----------------------
7. ግቢ ----------------------- -----------------------

**ለ. በ « ሀ» ስር ለተዘረዘሩት ቃላት በ «ለ» ስር ከተዘረዘሩት ውስጥ ተመሳሳያቸውን አዛምዱ**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ተቋዳሽ | ሀ. የተጣመረ |
| 2. ቁሳቁስ | ለ. ውጤቶች |
| 3. የተለመደ | ሐ ተካፋይ |
| 4. ምርቶች | መ. የተዘወተረ |
| 5. የተቆራኘ | ሠ. እቃዎች |

## ሐ.የሚከተሉትን እንስሳት ከስያሜዎች ጋር አዛምዱ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | አንበሳ | ሀ |  |
| 2 | ቀበሮ | ለ |  |
| 3 | የሜዳ ፍየል | ሐ |  |
| 4 | ዋልያ | መ |  |
| 5 | ሙስ | ሰ |  |

## ክፍል ሰድስት፡- ሰዋስው

የግስ እርባታ፡-

**ሀ. በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ግሶች ቅርጽ በመቀየር ዓረፍተ ነገሮቹን አሟሉ።**

ምሳሌ፡ አቶምሳ መኪናውን በፍጥንት __________ (መንዳት)
አቶምሳ መኪናውን በፍጥንት ነዳ ።

1. ዝናሽ ቁርሷን ______________________(በላ)
2. ናፍሬ ቡና______________________(ጠጣ)
3. ጫልቱ መልእክቷን በሰው__________________ (ላከ)
4. ትምህርት ቤት ቢረፍድብኝም ምሳዬን________________(በላ)
5. አንተ ልብሱን በደንብ ማጠብ _________________(አለ)

**ለ. የሚከተሉትን ቃላት በተሰጡት ባዶ ቦታዎች ላይ መርጣችሁ አሟሉ።**

| | | |
|---|---|---|
| ድግሪ | አለባቸው | ንጽሕናና |
| መቅረት | ሴት | ተሸለሙ |

1. በትምህርት ሰዓት መዘግየትም ሆነ __________ የስንፍና ምልክት ነው።
2. ቢሊሴ በህግ ትምህርት _______________አግኝታለች።
3. _______ ተማሪዎችን ዝቅ አድርጎ ማየት ተገቢ አይደለም።
4. ጥሩ ውጤት ያመጡ ተማሪዎች _______________ ።
5. የግል ___________መጠበቅ አስፈላጊ ነው።

## ክፍል ሰባት፡- ሥነ ጽሁፍ

### እቴ ሜቴ የሎሚ ሽታ

እቴ ሜቴ የሎሚ ሽታ
እናት አባትሽ ምን አሉሽ ማታ
ምንም ምንም ምንም አላሉኝ
ትምህርትሽን ተማሪ አሉኝ
ለማስተማር ቃልኪዳን ገብተው
ምለውልኛል ጋሻ ጦር ደፍተው
ከቤቴ በላይ ቁራ ሰፍሮ፤ ቁራ ሰፍሮ
የለችም ቢሉት ሄደ በሮ፤ ሄደ በሮ
እኔን ያብረኝ ያብረኝ ያብረኝ
የዝሆን ሀሞት ያስጠጣኝ ያስጠጣኝ
የዝሆን አሞት መራራ ነው መራራ ነው
የጎበዝ ልብ ተራራ ነው ተራራ ነው
ተራራ ሄጄ ስመለስ ስመለስ
አህያ ሞቶ ጅብ ሲያለቅስ ሲያለቅስ
ቁንጫ ቆማ ስትቀድስ ስትቀድስ
እባብ አንገቱ ሲነቀስ ሲነቀስ
የታረደው ሃምሳ ዶሮ የደረሰኝ አንድ ዶሮ
እሷን ይዤ ጓሮ ለጓሮ፡፡

(ስነጽሁፍ መሰረታዊያን፣57 ተሸሽሎ የተወሰደ)

## ተግባር

ሀ. ለሚከተሉት ጫዋታዎች ሂደታቸው በመከተል ተጫወቱ፡፡

1. ድብብቆሽ
2. የገበጣ ጫዋታ
3. ሌባና ፖሊስ

ማጠቃለያ

ክለሳ ጥያቄዎች

ሀ. የሚከተሉት ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ የሚኖራቸውን ትርጉም በዓረፍተ ነገር አሳዩ፡፡

1. ሰባ ------------------------------------------
2. ገና ------------------------------------------
3. ለጋ ------------------------------------------
4. መላ ------------------------------------------
5. ያድናል ------------------------------------------

ለ. ቅርስ ለአንድ ሀገር የሚሠጠውን ጥቅም በዝርዝር አብራሩ፡፡

ሐ. በአካባቢያችሁ የሚታወቁትን የእንስሳት ስም በመዘርዘር የቤትና የዱር እንስሳ በማለት ለዩ፡፡

መ. ከቤተሰባችሁ ውስጥ ለአንድ ሰው ደብዳቤ ጻፉ፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## ግብር ለሀገር ልማት

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-

- የውይይት ስርአትን ጠብቃችሁ ውይይት ታካሂዳላችሁ፡፡
  መምህራችሁ ቀርከሃ የሚለውን ምንባብ ሲያነብላቹ አዳምጣችሁ በቃል ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፡
- ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ ትፅፋላችሁ፡፡
- ግብር በሚል የቀረበውን ምንባብ ታነባላቹ ፡፡
- ከዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ምክንያትና ውጤት ለይታችሁ ትፅፋለችሁ፡፡
- ውጥን ታሪኮችን አጠናቃችሁ ትጽፋላችሁ፡፡
- ስርዓተ ነጥቦችን አይነትና ተግባር ለይታችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- አዎንታዊና አሉታዊ አረፍተ ነገሮችን ትለያላችሁ
- የልብ ወለድ አላባዊያንን ምንነት ትለያላችሁ
- የልብ ወለድ አላባዊያን የገፀባህርያትና የመቼትን ምንነት ትለያላቹ ምንነት ትለያላችሁ፡፡
- ተጠያቂያዊ ጥያቄዎችን ትመልሳላቹ ፡፡

### ክፍል አንድ ማዳመጥ

#### ቅድመ ማድመጥ

1. የቤታችሁ የተለያዩ ቁሳቁሶች ከምን ከምን የተሰሩ ናቸው?
2. በአካባቢያችህ የሚገኙት ቤቶች አጥር ከምን የተሰራ ነው ?

***ሀ. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ ቀርከሃ በሚል ርዕስ የቀረበውን ፅሁፍ ሲያነቡላችሁ በጥንቃቄ አዳምጡ፡፡ ከዚያም የቀረቡትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን ‹‹እውነት›› ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት በቃል መልሱ፡፡***

1. ቀርከሃ በኢትዮጵያ ከሚገኙ እፅዋት ውስጥ አንዱ ነው፡፡
2. በጥንት ጊዜ በሀገራችን ከቀርከሃ ባህላዊ የጦር መሳሪያ ይሰራ ነበር፡፡
3. ቀርከሃ በዘመናዊ መንገድ ማምረት በኢትዮጵያ የተለመደ ነው፡፡
4. ቀርክሃ ከአካባቢ ጥብቃ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት የለውም ፡፡
5. በአሁኑ ወቅት ከቀርከሃ የተለያዩ አይነት አልባሳትን መስራት ይቻላል፡፡
6. የቀርከሃ ምርት 70 በመቶ ከአፍሪካ ሀገራት በኢትዮጵያ ይገኛል ፡፡
7. በሀገራችን የቀርከሃ ክር ምርት በስፋት ይገኛል ፡፡

## ክፍል ሁለት መናገር

### ውይይት

ውይይት ጊዜና ቦታ ተወስኖለት፣ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ርእስ ጉዳዮች ላይ ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በጋራ ጉዳይ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሃሳባቸውን ለመለዋወጥና መግባባት ላይ የሚደርሱበት ነው፡፡

ተግባር

**ሀ. አንድ አዝናኝ የልጆች ፕሮግራም ከቴሌቪዥን ተከታትላችሁ ደግማችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡**

**ለ. በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በቡድን ውይይት አድረጉባቸው፡፡**

1. በትምህርታቸው ዝቅተኛ ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎች ውጤታቸውን ለማሻሻል ምን ማድረግ አለባቸው? ተወያዩበት፡፡
2. ሁልጊዜ የቤትና የክፍል ስራቸውን በጊዜና በአግባቡ የማይሰሩ ተማሪዎች ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል ? ተነጋገሩበት፡፡
3. በትምህርት ቤታችሁ ቤተ መጽሐፍት አለ? መልሳችሁ አዎ ከሆነ ለምን እና መቼ ትጠቀማላችሁ፡፡

## ክፍል ሦስት፡- ማንበብ

### ግብር

ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች፡፡

1. ግብር ምንድን ነው?
2. ግብር መክፈል ምን ጠቀሜታ አለው?
3. በግብር የሚሰበሰብ ገንዘብ ለምን ዓላማ ይውላል?

ግብርን በተገቢው ጊዜ መክፈል የስልጣኔ መገለጫም ነው፡፡ የሀገራት በእድገት የመለያየት ጉዳይና የዜጎች ለግብርና ታክስ ያላቸው የግንዛቤ ደረጃ አብሮ መታየት መቻል አለበት፡፡ የሰለጠኑ ሀገሮች ስለ ግብርና ታክስ ያላቸው ግንዛቤ ከታዳጊ ሀገሮች የተሻለ ሲሆን፣ እንደ ሀገራችን ስንቃኘው ስለ ገቢ ያለን ግንዛቤና የህግ ተገዥነት ዝቅተኛ ነው፡፡

ግብር ከፋዩ የግብር ህጎችንና በግብር አሰባሰብ አመራር መሰረት ተገቢውን ግብር መክፈሉን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ በቀደሙት ስርዓቶች የነበረው የግብር አሰባሰብ ስርዓት መሰረቱ በሰዎች መልካም ፈቃድ የሚሰበሰብ ነበር፡፡

## ጊዜ ንባብ

### እስከ አሁን ከንባቡ ምን ተረዳችሁ?

በሀገራችን የታክስ አሰባሰብ የተጀመረው በአክሱም ዘመነ መንግስት ነበር፡፡ የሚሰበሰበውም በገንዘብ ሳይሆን በአይነት የነበረ ሲሆን በጊዜ ሂደት የመንግስት ተቋም እየተጠናከረ ሲመጣ አሰራሩም ለውጥ አመጣ፡፡ የዘመናዊ ቀረጥ አሰባሰብ ስርዓት የተጀመረው በአጼ ምኒሊክ ዘመነ መንግስት ቢሆንም በአጼ ኃ/ስላሴ ዘመን አዋጅ ወጥቶለት ህግ ተረቆለት በደንብና ስርዓት ተደንግጎ ሲሰበሰብ በቅቷል፡፡

የግብር አሰባሰብ ስርዓቱ መከናወን ያለበት መንግስት ባመነበት ተመን መሰረት እንደሆነ ታምኖ በአይነት የነበረው በገንዘብ እየተቀየረ ከመምጣቱ ጋር የታክስ ማስከበሪያ ምጣኔውም 89 በመቶና ከዚያ በላይ ይሰበሰብ እንደነበር የገቢ ጣሪያው በመስፋቱ ሰዎች ሰርተው መገበር ብቻ በሆነበት አሰራር ፋይዳው አነስተኛ ነበር፡፡ በሂደት የታክስ ማሻሻያ ስርኣት ወጥቶለት የታክስ ጣሪያው ተሻሽሎ በግለሰብ በቀጥተኛ ታክስ 35 በመቶ፣ ካምፓኒ 30 በመቶ እንዲከፍል ተደርጎ የአሰባሰብ ስርዓቱም በተማከለ አሰራር እንዲከናወን ተደርጓል፡፡

የገቢ ግብር አሰባሰብ ስርዓቱ ዘመናዊ አሰራርን ያልተከተለ በነበረበት አሰራር ሰዎች በአግባቡ ያልተዋቀሩና ተገልጋዮቹም በተለያየ መንገድ የሚጉላሉበት ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ በዘመናዊ አሰራር መሰረት የንግድ ስርዓት ውስጥ ያለውን የገቢ ግብር፣ በደሞዝተኛ፣ የኪራይ ግብርና በማዘጋጃ ቤት የገቢ ግብሮች ይሰበሰባሉ፡፡ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ መጀመሩ ዘመናዊ አሰራር ለመከተልና ለመጠቀም ስለሚያስችልና ስራን ለማቀላጠፍ እንዲሁም የገቢ ግብር መጠንን ለሚደብቁ ትክክለኛውን ገቢና ወጪ አውቆ አሰባሰቡ እንዲከናወን ስለሚረዳ ነው፡፡

ለአብነት የግብር አሰባሰብ ስርዓቱን መሰረት ከማስያዝ አንጻር አዲስ አበባ በራሷ ገቢ የምትተዳደር በመሆኗ የገቢ ስርዓቱ ጠንካራ አሰራርና ዘመናዊነትን በተከተለ መልኩ መሰራቱን ማሳያ ነው፡፡ በከተማዋ 14 የተለያዩ ቅርንጫፎች 116 የማይክሮ ፋይናንስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በመክፈት ተገልጋዩ በቅርበት ሊስተናገድበት የሚችልበት አሰራር ተዘርግቶ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ተደራሽነት ባለው የግብር አሰባሰብ ስርአት መሰረቱ ግብር ከፋዩ ሂደቱን እንደ ግዴታ ሳይሆን ግብር መክፈሉ ከተማዋን ለመለወጥ ከሚኖረው ጠቀሜታ አንጻር እንዲወስድ በተደረገው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስርአት የአመለካከት ለውጥ እየመጣና ግብር መክፈሉ የዜግነት ግዴታ መሆኑ በህብረተሰቡ እየሰረፀ ይገኛል፡፡

ምንጭ፡- (አዲስ ዘመን ጋዜጣ የካቲት 2010) ዳሎቻ ወረዳ ገቢዎች ባ/ቅ/ጽ/ቤት)

### ተግባር

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ ማብራሪያ ስጡ፡፡**

1. አንድ ዜጋ ግብር የመክፈል ግዴታ የተጣለበት በምን ምክንያት ነው?
2. ግብር መክፈል ምን ጠቀሜታ አለው?
3. በቀድሞውና በዘመናዊው የግብር አሰባሰብ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
4. ግብር መሰብሰብ የተጀመረው መቼ ነው? እንዴት ነበር?
5. ዜጎች ግብር ባይከፍሉ ምን አይነት ነገር ይከሰታል?

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነውን ‹‹አውነት›› ስህተት የሆነውን ‹‹ሀሰት›› በማለት በምክንያት አስደግፋችሁ መልሱ፡፡**

1. ግብር በተገቢ መንገድ መክፈል የስልጣኔ መገለጫ ነው፡፡
2. ያደጉት ሀገራት ስለ ግብርና ታክስ ያላቸው ግንዛቤ ጥሩ ነው፡፡
3. በሀገራችን የታክስ አሰባሰብ የተጀመረው በደርግ ዘመን ነበር፡፡
4. በአዲስ አበባ ከተማ 14 የተለያዩ የግብር መሰብሰቢያ ቅርንጫፎች አሉት፡፡
5. ግብር መክፍል የዜጎች ግዴታ ነው፡፡

**ሐ. በ «ሀ» ስር የተዘረዘሩትን ቃላት በ «ለ» ስር ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይ ፍቺ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. መልካም ፍቃድ | ሀ. ስረዓት |
| 2. ደንብ | ለ. በሁሉም ቦታ |
| 3. ተደራሽነት | ሐ. ፍላጎት |
| 4. ገንዘብ | መ. ብር |
| 5. ጠንካራ | ሠ. ብርቱ |

**መ. በ «ሀ» ስር የተዘረዘሩትን ቃላት በ «ለ» ስር ከተዘረዘሩት በምንባቡ መሠረት ተቀራኒ ፍቺ አዛምዱ ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ገቢ | ሀ. ጥንታዊ |
| 2. ዘመናዊ | ለ. ሩቅ |
| 3. ዝቅተኛ | ሐ. ከፍተኛ |
| 4. ቅርብ | መ. ወጭ |
| 5. ጠቀሜታ | ሠ. ጉዳት |

## ክፍል አራት፡- መፃፍ

### ተግባር

**ሀ. ግብር የሚለውን ምንባብ መነሻ በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በፅሁፍ መልስ ስጡ፡፡**

1. የምንባቡ የመጀመሪያ አንቀፅ ስለምን እንደሚናገር በራሳችሁ አባባል በአጭሩ ፃፉ፡፡
2. ከግብር የሚሰበሰብ ገንዘብ ምን ይሰራበታል? በሁለት አንቀፅ ፅፋችሁ አቅርቡ፡፡

## ምክንያት እና ውጤት

ምክንያት ማለት ለአንድ ድርጊት መፈጸም መንስዔ የሚሆን ሃሳብ ሲሆን፤ ውጤት ደግሞ መንስዔ ተከትሎ የሚመጣ ግኝት ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ፉላሳ በፍጥነት ሲሮጥ እንቅፋት መታው፡፡

ምክንያት፡- በፍጥነት መሮጥ

ውጤት፡- በእንቅፋት መመታት፡፡

**ለ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ምክንያትና ውጤት ለይታችሁ ጻፉ፡፡**

1. የቤት ስራ ባለመስራቱ አባቱ ተቆጣው፡፡

ምክንያት ______________________ ውጤት______________________

2. እናቷ ስለታመመች ከትምህርት ቤት ቀረች፡፡

ምክንያት ______________________ ውጤት______________________

3. የሀኪም ምክር ስለማትሰማ ዘወትር ትታመማለች፡፡

ምክንያት ______________________ ውጤት______________________

4. ጥላሁን ሲናገር እሰማዋለሁ፤ምክንያቱም ምክሩ ደስ ይለኛል፡፡

ምክንያት ______________________ ውጤት______________________

5.በህጻንነቱ ትምህርት ቤት በመግባቱ ፊደል ለመለየት ጊዜ አልወሰደበትም፡፡

ምክንያት ______________________ ውጤት______________________

## ውጥን ታሪክ መጨረስ

ሐ. የሚከተለውን ውጥን ታሪክ በራሳችሁ አባባል ጨርሱ፡፡

## ያልጠለቀች ጀምበር

ወይዘሮ ባንቺይፍሩ ከሃብታም ቤተሰብ የተወለዱ ናቸው፡፡ ከተወለዱ ዕለት ጀምረው አልታመሙም፡፡ የተቸገረ ሰው ሲያዩ ያለቅሳሉ፡፡ አሳዘኝ ዜና ከሰሙ ሌሊት እንቅልፍ የላቸውም፡፡ ተማሪ እያሉ ዘወትር ለትራንስፖርት የሚሰጣቸውን ብር በአውቶቢስ እየሄዱ ቀሪ ሳንቲም ጉሊት ቁጭ ብሎ ምጽዋት ለሚጠይቀው…

### ክፍል አምስት፡-ቃላት

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንደ የአጠያየቃቸው መልሱ፡፡**

1. አዝርዕት ይዘራል ካለ ችግኝ -------- ይባላል ፡፡

   ሀ. ይታፈሳል ለ. ይበተናል ሐ. ይነቀላል መ. ይተከላል

2. ለዶሮ እሽ ካለ ለድመት ------ ይላል፡

   ሀ. ብስ ለ. ክፍ ሐ. ውሽ መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው፡፡

3. ለሰው ነፍሰጡር ካለ ለላም------ ይላል፡፡

   ሀ. ክበድ ለ. ጥገት ሐ. እርጉዝ መ. ሁሉም

4. ወፍ ብሎ ጎጆ ካለ ዶሮ ብሎ ----ይላል፡፡

   ሀ. ቆጥ ለ. ቤት ሐ. ዛፍ መ. ጎጆ

5. ለከብት በረት ካለ ለፍየል ------ ይላል፡፡

   ሀ. ጋጥ ለ. ጓዳ ሐ. በረት መ. ጉረኖ

**ለ. የሚከተሉትን አባባሎች በምሳሌው መሰረት አሟሉ፡፡**

ምሳሌ፡- ዋሽንት --- ይነፋል

1. ከበሮ ----------
2. መስንቆ ---------
3. በገና ----------
4. ነጋሪት --------
5. መለከት -------

**ሥርአተ ነጥቦች ፡- በወረቀት ላይ የሰፈረ ሐሳብ መልዕክቱ ግልፅ ሆኖ እንዲተላለፍ ሥርአተ-ነጥቦች የጎላ ድርሻ አላቸው፡፡ በፅሁፍ ላይ ነጥቦችን አስተካክሎ ካለመጠቀም የተነሳ ዐ-ነገሮች ያሻማሉ ፡ መልዕክቶች ይዛባሉ፡ ሀሳቦች ግልፅ አይሆኑም**

**ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው**

**የስርዓተ ነጥብ አይነቶች፡-** ስርአተ ነጥቦች የፅሁፍ መሪ ምልክቶች በመባል ይታወቃሉ በንግግር ወቅት በአካል እንቅስቃሴ አፅንኦት እንደምንሰጥ ሁሉ በፅሁፍ ወቅት ደግሞ ስርአተ ነጥቦች መሪ ምልክቶች በመሆን ያገለግላሉ

**1. አንድ ነጥብ (ይዘተ) (.)፡-**በምህፃረ - ቃል አሳጥሮ ለመጻፍ ያገለግላል፡፡

ለምሳሌ፡ ተ. መ. ድ. = የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት

- ብርና ሳንቲሞችን እንዲሁም ሙሉና ክፍልፋይ ቁጥሮችን ለመለየት

ምሳሌ፡ 9.50 = ዘጠኝ ብር ከሃምሣ ሳንቲም

1.9 = አንድ ነጥብ ዘጠኝ

**2.ሶስት ነጥብ / ነጠብጣብ/ (. . .) ፡-** የተዘለሉ ሀሳቦች ሲኖሩ እና ወደ ፊት የቀረ ሀሳብ መኖሩን ለማሳወቅ ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- እንደ ወንበር፣ አልጋ፣ ጠረጴዛ .... ብዙ ብር አውጥቶ ገዛ፡፡

3 .አራት ነጥብ(።)፡- እርግጠኛና ቀጥተኛ የሆኑ ጉዳዮች በዓርፍተ - ነገር ተጽፈው ሙሉ ዕረፍት ሲደረግና ሐሳቡም ሲቋጭ መደምደሚያ ሆኖ ይገባል።
ለምሳሌ፡- መምህሩ ተማሪዎቹን ከልብ ያስተምራል።

4. ጥያቄ ምልክት (?)፡- አንድን ሀሳብ በጥያቄ መልክ ለማስተላለፍ ያገለግላል።
ለምሳሌ፡- የቤት ሥራህን ሠርተሃል?

5. ቃለ አጋኖ (!)፡- አንድ የተፈጸመን ድርጊት በአግርሞት መግለጽ ነው።
ለምሳሌ፡- አቤት ! መኪናው አመድ ሆነ።

6. ድርብ ትዕምርተ ጥቅስ (‹‹ ››) ፡-ይህ ሙሉ የጥቅስ ምልክት በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊያገለግል ይችላል።

ሀ. ጸሐፊው ሐሳቡ ከራሱ የፈለቀ አለመሆኑን ለማመልከት ምሳሌ፡ “ሥራ ለሠሪው እሾህ ላጣሪው” ሲባል አልሰምህም?

ለ. የሁለት ሰዎችን ምልልሳዊ ንግግር ለየብቻ በጥቅስ ለይተው ለማሳየት ምሳሌ፡

“ዛሬ ትምህርት ቤት ሄደሃል?”

“አዎና! ግን ለምን ጠየቅከኝ?”

“የትራንስፖርት ችግር ስለነበረ”

**ሀ.በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ተገቢውን ሥርዓተ ነጥብ አሟልታችሁ ፃፉ።**

1. የሚኮርጅ ተማሪ የፈተና ውጤቱ ዜሮ ይሆናል
___________________________________
2. ኤድስ መድኃኒት ያልተገኘለት በሽታ ነው ብሎ ሬዲዮ ተናገረ
___________________________________
3. ዛሬ የተማርነው በጣም መወፈር ለጤና ጠንቅ ነው የሚል ነው
___________________________________
4. መኮረጅ አይጠቅምም በርትታችሁ ሥሩ አሉ ርዕሰ መምህሩ
___________________________________
5. ደብተሬን ነጠቁኝ ብሎ የነገረኝ ልጅ ወዴት ሄደ

**ለ. ቀጥለው የተዘረዘሩትን ቃላትና ሀረጋት በተጓደሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በማስገባት አሟሉ።**

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. እንዳይጠቃ | 2. ብቃት | 3. የበለጸጉ | 4. አሟልቶ |
| 5. የዕለት ተዕለት | 6. ጥንካሬ | | |

1. ------------ ተግባርን ለማከናወን ጤነኛ መሆን ያስፈልጋል።
2. በማዕድን --------- ምግቦች ጤናማና ጠንካራ ያደርጋሉ።
3. ወተት ሶስቱን የምግብ አይነቶች ---------- የያዘ ምግብ ነው።
4. ሰውነታችን በበሽታ ----------- ተመጣጣኝ ምግብ መመገብ ያስፈልጋል።
5. ዘወትር የአካል -------- እንቅስቃሴ ማድረግ ሰውነትን ለማጠንከር ይጠቅማል።
6. ካልሲያም ያላቸውን ምግቦች መመገብ አጥንት ------ እንዲኖረው ያደርጋል።

**ሐ. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች አሉታዊ ወይም አዎንታዊ በማለት ለዩ።**

1. የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ታታሪዎች ናቸው። ______________________
2. ሀገሪቱ በከባድ አዘቅት ውስጥ ትገኛለች። ____________________________
3. የመሃንዲሶቹ የስራ እቅድ አያስደስትም። ______________________
4. ከጥዋት እስከ ማታ በመንገድ ላይ በርካታ ተሽከርካሪዎች ይመላለሳሉ። ______
5. በየዕለቱ አዳዲስ ወሬዎች አይሰሙም። __________________

**መ. በሚከተሉት ቃላት ላይ ያሉትን መነሻ እና መድረሻ ቅጥያዎችን ለዩ።**

| | <u>መነሻ ቅጥያ</u> | <u>መድረሻ ቅጥያ</u> |
|---|---|---|
| 1. እንደነገርኩህ | __________________ | ______________________ |
| 2. ስለፈለገች | __________________ | ______________________ |
| 3. አጠራህ | __________________ | ______________________ |
| 4. በወጣቶች | __________________ | ______________________ |
| 5. አስመሰከሩህ | __________________ | ______________________ |

## ክፍል ሰባት፡- ስነ-ፅሁፍ

### የልቦለድ አላባውያን

ዓላባዊያን ማለት ልቦለዱን ለመፃፍ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች ናቸው፡፡

የልቦለድ ዓላባዊያን 7 ሲሆኑ ለዚህ ክፍል ገፀባህሪያትንና መቼትን ብቻ እናያለን

1. ገፀ ባህርያት፡- ማለት በልቦለድ ፅሁፍ ውስጥ ያሉ የገሃዱ ዓለም ሰዎች ነጸብራቅ ናቸው፡፡
2. መቼት፡- ማለት ድርጊቱ መቼ እንደተፈፀመ ጊዜውንና፤ የት እንደተፈፀመ ቦታውን ይገልፃል፡፡

ተግባር

**ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምርጡ፡፡**

1. ከሚከተሉት ውስጥ የስነ ፅሁፍ አይነት የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ቃላት ለ. ልቦለድ ሐ ሀረጋት መ ቋንቋ
2. የገሀዱን ዓለም ሰዎች ወኪል የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ገፅ ባህርያት ለ. መቼት ሐ. ጭብጥ መ. ግጭት
3. በአንድ ልቦለድ ውስጥ ጊዜና ቦታን የሚያሳይ የቱ ነው?
   ሀ. መቼት ለ. ጭብጥ ሐ. ግጭት መ. መልስ የለውም
4. በልቦለድ ውስጥ ገጸ ባህርያት የኖሩበት ዘመን የሚገለጽበት የቱ ነው?
   ሀ ታሪክ ለ. ግጭት ሐ. መቼት መ. ትልም
5. በልቦለድ ውስጥ ገጸ ባህርያት የኖሩበት ቦታ የሚገለጽበት የቱ ነው?
   ሀ ትልም ለ. ግጭት ሐ. ታሪክ መ. መቼት

## ክለሳ ጥያቄዎች

### ሀ. የሚከተሉትን ስሞች በምህፃረ ቃል ፃፉ፡፡

1. የአፍሪካ ህብረት
2. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት
3. የአዲስ አበባ ንግድ ኢንዱስትሪ ቢሮ
4. የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር
5. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን

### ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቡድን በቡድን ተወያይታችሁ በቃል መልሱ፡፡

1. ልቦለድ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የልቦለድ አላባዊያን በመዘርዘር ምንነታቸውን አስረዱ፡፡
3. በምታውቁት ተረት ውስጥ ያሉ እንስሳቶችን ዘርዝሩ፡፡

### ሐ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ምክንያትና ውጤት ለይታችሁ ፃፉ፡፡

1. ልጁ የፈላ ውኃ ስለተደፋበት እጁ ነፈረ፡፡
2. ሹፌሩ ጠጥቶ በፍጥነት በማሽከርከሩ መኪናው ተገለበጠ፡፡
3. ብዙ ዝናብ በመዝነቡ የአባይ ግድብ ሞላ፡፡
4. ዘወትር ስለሚያጠና የፈተናው ውጤት ከፍተኛ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

## አጥንት

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡.

- የቀረበላችሁን ምንባብ አንብባችሁና አድምጣችሁ ለጥያቄዎች መልስ ትሰጣላችሁ፡፡
- የክርክር አቀራረብና ሂደቶችን ትገልፃላችሁ፡፡
- የቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ ትፅፋላችሁ፡፡
- ታዋቂ ስሞችን አሳጥራችሁ ትፅፋላችሁ፡፡
- በተሰጣችሁ ርዕስ መሰረት አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡
- ውጥን አረፍተ ነገሮችን ታሟላላችሁ፡፡
- በአያያዥ ቃላት ዐረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡
- ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን አጣምራችሁ ትጽፋላችሁ፡፤
- በክፍል ውስጥ ግጥም ታነባላችሁ፡፡
- ከግጥሙ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ ትሰጣላችሁ፡፡

### ክፍል አንድ ማዳመጥ

#### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በእረፍት ቀን ምን ምን ተግባር ታከናውናላችሁ? ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
2. እናንተ ስለአንድ አንድ ጉዳዮች መረጃ ከየት ታገኛላችሁ? እርስ በራሳቸው ተነጋገሩበት፡፡

**ሀ. መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ ቴሌቪዥን በሚል ርዕስ የቀረበውን ፅሁፍ ሲያነቡላችሁ በጥንቃቄ አድምጡ፡፡ ከዚያም የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. ቴሌቪዥን ምን አይነት መሳሪያ ነው?
2. ለመጀመሪያ ጊዜ ቴሌቪዥን መቼና በማን ተሰራ?
3. ቴሌቪዥን የሚለው ቃል ከምን ቃል የመጣ ነው? ትርጓሜውስ?

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

1. ቴሌቭዥን የምን እና የምን ማሰራጫ ዘዴ ነው?

ሀ የፎቶ ብቻ ለ. የምስልና የድምፅ ሐ. የምስል ብቻ መ. የድምጽ ብቻ

2. የመጀመሪያ የቴሌቭዥን መግለጫ የተሠጠው መቸ ነው?

ሀ. 1918 ለ. 1818 ሐ 1925 መ. 1926

3. በጀርመን ሀገር የኦሎፒክ ውድድር በቴሌቪዥን የተሰራጨው መች ነው?

ሀ. 1930 ለ. 1936 ሐ. 1940 መ. 1950

4. የመጀመሪያ የከለር ቴሌቭዥን ስርጭት ሙከራ የተደረገው መች ነው?

ሀ. 1940 ለ. 1840 ሐ 1888 መ. 1900

ክፍል ሁለት መናገር

## ክርክር

ክርክር በሁለት የተለያየ ሃሳብ ያላቸው ቡድኖች መካከል የሚደረግ ስርዓት ያለው ሙግት ነው።

በክርክር ወቅት የሚያስፈልጉ ነገሮች የመከራከሪያ ርዕስ ጉዳይ፣ ተከራካሪ ቡድኖች፣ ዳኛና ታዛቢዎች ናቸው። በክርክር ወቅት ሊደርጉ የሚገባቸው ነጥቦች:-

1. ማስታወሻ መያዝ
2. በትህትና መናገረ
3. የርዕሰ ጉዳዩን ሂደት መጠበቅ እና የዳኞችን ውሳኔ መቀበል።

**ሀ. በአከባቢያችሁ ለአቅመ ደካሞች ምን አይነት ድጋፍ ይደረግላቸዋል። በክፍል ውስጥ ሃሳባችሁን ተለዋወጡ።**

ለ. የምትኖሩበትን አካባቢ ስያሜ ቤተሰባችሁን ጠይቃችሁ በክፍል ውስጥ ተናገሩ።

**ሐ. ከሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች አንዱን መርጣችሁ በክፍል ውስጥ ክርክር አድርጉ።**

1. ገጠር መኖር ወይስ ከተማ መኖር የሚሻለው የቱ ነው?
2. በፈረቃ መማር ወይስ ሙሉ ቀን መማር የቱ ይሻላል?
3. ከዘመናዊና ከባህላዊ ፍትህ ስርአት የቱ ይሻላል?

## ክፍል ሦስት፡- ማንበብ

# የአጥንት ጥንካሬ

### ተግባር

### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

1. አጥንት ምንድን ነው?
2. አጥንት ለሰውነታችን ምን ጠቀሜታ አለው?
3. የሰዎችና የእንስሳት አጥንት ልዩነት አላቸው?
4. ከስዕሎቹ ምን ትረዳላቹ ? ተወያዩበት



አጥንት ከፍተኛ የሆነ ጫና የመቋቋም፣ ጭነት የመሸከምና የመለጠጥ አቅም ያለው አስደናቂ የምሕንድስና ውጤት እንደሆነ ይገለጻል፡፡ የሰው ልጅ አፅም በግምት 206 በሚያህሉ አጥንቶችና 68 በሚያህሉ መገጣጠሚያዎች የተዋቀረ ነው፡፡

በሰውነታችን ውስጥ ረጅሙ አጥንት የጭን አጥንት ሲሆን ከሁሉም የሚያንሰው ደግሞ በጆሯችን ውስጥ የሚገኘው አጥንት ነው፡፡ ጥሩ ችሎታ ያላቸው ስፖርተኞች ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ በግልጽ መመልከት እንደሚቻለው በሰውነት ውስጥ ያሉት አጥንቶች፣ ጡንቻዎች፣ ለስላሳ አጥንት (ካርቲሌጅ) እንዲሁም መገጣጠሚያዎች አንድ ላይ ተቀናጅተው ጤናማ የሆነ አካል በጣም አስደናቂ የሆነ እንደ ልብ የመተጣጠፍ ችሎታ እንዲኖረው ያደርጋሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በሰውነታችን ውስጥ ያሉት አጥንቶች በጣም ከፍተኛ የሆነ ጭነት መሸከም ይችላሉ፡፡ አጥንት የተሠራው ልክ የብረት አርማታ በሚሠራበት መንገድ ነው፡፡ አርማታ ውስጥ የሚገባው ብረት አርማታው ጫና መቋቋም የሚያስችል ጥንካሬ እንዲኖረው ሲያደርግ ሲሚንቶው፣ አሸዋውና ጠጠሩ ደግሞ ከፍተኛ ጭነት የመሸከም ኃይል እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ይሁን እንጂ አጥንት ያለውን ጭነት የመሸከም ኃይል ከሁሉ የተሻለ የሚባለው ባለ ብረት አርማታ እንኳ አይስተካከለውም፡፡

ከአርማታ በተለየ መልኩ አጥንት፣ ቁጥር ስፍር የሌላቸው ሕያዋን ፍጥረታት አካል አብይ ክፍል ነው። ደግሞም በድን አይደለም። ራሱን መጠገን የሚችል ከመሆኑም ሌላ እድገቱን ለሚቆጣጠሩ ሆርሞኖች ምላሽ ይሰጣል፤ አልፎ ተርፎም የደም ሴሎችን በማምረት ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

በተጨማሪም ልክ እንደ ጡንቻ የሚያርፍበት ጭነት እየጨመረ ሲሄድ ቀስ በቀስ ይበልጥ እየጠነከረ ይሄዳል። ከወንበር ወንበር ሲገላበጡ ከሚውሉ ሰዎች ይልቅ ስፖርተኞች ጠንካራ አጥንት የሚኖራቸው በዚህ ምክንያት ነው።

(ምንጭ፡- https://p.dw.com/p/1Edck ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ)

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ።**

1. አጥንት ለምን ይጠቅማል?
2. ከሰውነታችን ትልቅ እና ትንሹ አጥንት የተባሉት የትኞቹ ናቸው?
3. ለሰው ልጅ ስፖርት መስራት ምን ጠቀሜታ አለው?

ለ. በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምርጡ።

1. የሰው ልጅ አጥንት በግምት ስንት ይሆናሉ?

   ሀ. 206 ለ. 106 ሐ. 306 መ. 406

2. የሰው ልጅ አጥንት መገጣጣሚዎች ስንት ናቸው?

   ሀ. 58 ለ. 68 ሐ. 78 መ. 88

3. ከሰውነታችን ረጅሙ አጥነት የቱ ነው?

   ሀ. የጀሮ ለ. የጭን ሐ. የጡንቻ መ. የእጅ

4. ከሌላው የተሸለ ጠንካራ አጥንት ያላቸው ሰዎች እነማን ናቸው?

   ሀ. ሽማግሌዎች ለ. ልጆች ሐ. ስፖርተኞች መ. ወጣቶች

5. ቁልፍ ሚና ይጫወታል። የተሰመረበት ቃል ፍቺ ማለት ምን ማለት ነው?

   ሀ. የሚሮጡ ለ. የሚተኙ ሐ. ትልቅ ድርሻ መ. የሚቆሙ

**ሐ. በ «ሀ» ስር ለተዘረዘሩት ቃላት በ «ለ» ስር ከተዘረዘሩት ጋር በተመሳሳይ ፍቺ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ለስላሳ አጥንት | ሀ. ሽክም |
| 2. ሀይል | ለ. የተለየ |
| 3. ሚና | ሐ. ድርሻ |
| 4. ጭነት | መ. ከርትሌጅ |
| 5. የተሻለ | ሠ. ጉልበት |

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

**ሀ. የሚከተሉትን የመስሪያ ቤት ስሞችን በምህፃረ ቃል ፃፉ፡፡**

1. የፌደራል እንባ ጠባቂ ኮሚሽን -------------------------------
2. የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት --------------------------
3. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ---------------------------------
4. የኢትዮጵያ ባህልና ቱሪዝም ፌደሽን ---------------------------------
5. የታክሲ ባለንብረቶች ማህበር ----------------------------

**ለ. ከዚህ በታች የቀረቡት አካል ጉዳታኞችን ከሚደግፉ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱን መርጣችሁ ጠቀሜታውን በሁለት አንቀጽ ፅፋችሁ አቅርቡ፡፡**

1. ዊልቸር
2. ነጭ በትር
3. የምልክት ቋንቋ
4. ብሬን

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ማዛመድ

ተግባር

**ሀ. በ « ሀ» ስር ለተዘረዘሩት ቃላት በ «ለ» ስር ከተዘረዘሩት ውስጥ ተመሳሰይ ፍቺ አዛምዱ**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሌት ተቀን | ሀ. ዋና |
| 2. አውራ | ለ. መንገድ |
| 3. ጎዳና | ሐ. ማሾፍ |
| 4. ማፌዝ | መ. መከራ |
| 5. ስቃይ | ሠ. መፈለግ |
| 6. አብነት | ረ. ምሳሌ |
| 7. መሻት | ሰ. ዘውትር |

**ለ. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ወደ ነጠላ ቁጥር ቀይሩ፡፡**

**ለምሳሌ፡- ቀያይ ቀይ**

1. ደጋግ ______________________________
2. ጥቋቁር ______________________________
3. መጽሐፍት ____________________________
4. ጎዳናዎች _____________________________
5. ቃላት ______________________________

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋሰው

### ተግባር

**ሀ. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ተስማሚውን በመምረጥ ዓረፍተ ነገሮቹን አሟልታችሁ ፃፉ፡፡**

| ሊ- ልቦለድ | ገለፃ | ብክለት | ሳይንሳዊ | ግብዣ |
|---|---|---|---|---|

1. በ __________ የተደገፈ ጭውውት ጠቀሜታው አያከራክርም፡፡
2. የፈጠራ ስራ የማይጫነው የፅሁፍ አይነት ________ በመባል ይታወቃል፡፡
3. __________ ስላለባት ሽር ብትን ብለ ወጣች፡፡
4. __________ ምርምር የሰው ልጅ አኗኗር እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡
5. ማንኛውም ዜጋ የውሃን _________________ መከላከል አለበት፡፡

**ለ. የሚከተሉትን አጫጭር ዓረፍተ ነገሮች በአንድ ላይ አጣምራችሁ ፃፉ፡፡**

ለምሳሌ፡- ወርቂቱ ጉበዝ ናት፡፡

ወርቂቱ ዛሬ ተሸለመች፡፡

ወርቂቱ ጎበዝ ስለሆነች ዘሬ ተሸለመች፡፡

1. ዛፍ ትልቅ ነው፡፡
   ዛፍ ቤት ላይ ወደቀ፡፡
   _______________________________________________
2. አስቴር ፓይለት ናት፡፡
   አስቴር የፈለገችውን ሀገር ትጎበኛለች፡፡
   _______________________________________________
3. ገበያተኞች ወደ ገበያ ሄዱ፡፡
   ገበያተኞች እህል ገዝተው ተመለሱ፡፡
   _______________________________________________

4. ወታደር ከበደ የትራፊክ ፖሊስ ነው፡፡
   በመንገድ ላይ ሥነ ሥርዓትን ያስከብራል፡፡

   ---

5. ብዙ ተማሪዎች ተሰልፈው ተራ ይጠብቃሉ፡፡
   በዚህ መስመር የአውቶብሶች ቁጥር አነስተኛ ነው፡፡

   ---

ክፍል ሰባት፡- ስነ-ፅሁፍ

**ሀ የሚከተለውን ግጥም በክፍል ውስጥ ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ ተራ በተራ አንብቡ፡፡**

## ፊደል

የሀሳብ መግለጫ የንግግር ቁልፍ

የመተዋወቂያ የጥበብ በራፍ ፡፡

መገናኛ መንገድ አይነቱ የበዛ

ከሰው ልጅ መግባቢያ ትርጉም የሚነዛ

የአለም መክፈቻ የፍጥረት ብረሃን

የሚያነጋግር ነው መስመር ቴሌፎን ፡፡

የሰማይ ምርመራ የመሬት የባህር

የመሃንዲስ ስራ ሌላም ብዙ ሚስጥር

የቅኔ የዜማ ደግሞም የሙዚቃ

የአቶም ምርመራ ጉዞ የጨረቃ

መግለፅ ይቻላል በፊደል ምልክት

ትርጉሙን ይሰጣል ለተመራመሩት፡፡

በቦታው ሲገባ ቃል ሆኖ ሲጠራ

እንዲህ ነው በማለት መንገድ የሚመራ

ታሪክ ነው ለትውልድ የሚተላለፍ

ፊደል ነው መሰረት የሚሆን መጽሐፍ፡፡

ምንጭ፡- ገብረክርስቶስ ደስታ 1998፣ስብስብ ግጥሞች ለማስተማሪያ

ተደርጎ የተሸሻለ፡፡

**ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሰረት መልሱ፡፡**

1. ግጥሙ ስንት መስመር አለው?
2. የግጥሙ የመጨረሻ መስመር የመጨረሻው ቃል ምን የሚል ነው?
3. የግጥሙ የመጀመሪያ መስመር የመጨረሻው ቃል ምን የሚል ነው?
4. የግጥሙ ርዕስ ምንድን ነው ?

**ሐ. ከላይ የቀረበውን ግጥም ስለምን ይናገራል፡፡ ሀሳብን ግለጹ፡፡**

## ማጠቃለያ
## ክለሳ ጥያቄዎች

1. **የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተገቢው ሁኔታ አብራሩ፡፡**

    1. ክርክር ምንድን ነው
    2. አሳጥሮ መጻፍ ማለት ምን ማለት ነው

2. **የሚከተሉትን በነጠላ ቁጥር የቀረቡትን ቃላት ወደ ብዙ ቁጥር አመልካች ቀይራችሁ ጻፉ፡፡**

    1. ቃል
    2. ሀረግ
    3. መምህር
    4. ገበሬ
    5. ኃይል

3. **በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

    1. በግ
    2. አስደናቂ
    3. ጥናት
    4. መጠገን
    5. ሀገር

# ምዕራፍ ስምንት

## የአመጋገብ ስርዓት

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡.

- የአመጋገብ ስርአት ትገነዘባላችሁ፡፡
- ለተለያዩ ቃላት ዓውዳዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ታዋቂ የመስሪያ ቤት ስሞችን አሳጥራችሁ ትጽፋላችሁ፡፡
- ራስችሁን ለሌሎች ተማሪዎች ታስተዋውቃላችሁ፡፡
- የአመጋገብ ስርዓትን የሚያሳዩ ስዕሎችን አይተው ምንነታቸውን ይናራሉ፡፡
- የሰዋስው ስርአት ጠብቃችሁ አረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ ፡፡
- የቃላት እርባታ ትናገራላችሁ፣ ትፅፋላችሁ ፡፡
- የገረፍታ ንባብ ምንነት ትረዳላችሁ፡፡
- ለፈሊጣዊ ንግግሮች አቻ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- የቃላዊ ግጥም አይነቶችን ትናገራላችሁ፡፡

### ክፍል አንድ ማዳመጥ

#### ቅድመ ማዳመጥ

1. በጋራ መመገብ እንዴት ይቻላል?
2. ልጆች ከቤተሰብ ጋር መመገብ ያለባቸው መች ነው?
3. ለልጆች ከቤተሰብ ጋር መመገብና በተናጠል መመገብ የቱ ይሻለል?

ሀ) መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ በጋራ መመገብ በሚል ርዕስ የቀረበውን ፅሁፍ ሲያነብላችሁ በጥንቃቄ አዳምጡ፡፡ ከዚያም የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. ልጆች ከቤተሰባቻው ጋር መመገብ ምን ጠቀሜታ አለው?
2. ልጆች ብቻቸውን በመመገባቸው ምክንያት ምን ጉዳት ይደርስባቸዋል?
3. አብሮ በመመገብ ከቤተሰብና ከልጆች ተጠቃሚው ማን ነው?
4. ከሰዎችጋር አብረን ስንመገብ ምን ማድረግ አለብን?

5. ከዳመጣችሁት ምንባብ ምን ተማራችሁ?

**ለ. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል የሆነውን እውነት ስህተት የሆነውን ሀሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. በአንድ ማዕድ መመገብ ለልጆች ስነ- ልቦና ጥሩ ነው፡፡
2. በጥንት ዘመን ልጆች ከወላጆች ጋር እንዲመገቡ አይፈቀድም፡፡
3. ልጆችና ወላጆች በጋር መመገብ አስቸጋሪ ነው፡፡
4. ወላጆች እና ልጆች አብረው መመገባቸው ጥቅም አለው፡፡
5. ቤተሰብ በአንድነት ቴሌቭዥንና ሬድዮ ፕሮግራሞችን ይከታተላሉ፡፡


## ክፍል ሁለት፡- መናገር

1. የምታውቁትን ባህላዊ ምግቦችን በመዘርዘር የአንዱን አሰራር አስረዱ፡፡
2. በአከባቢያችሁ በበዓላት ወቅት የሚሰሩ ባህላዊ ምግቦች ምን ምን ናቸው?
3. በቤት ውስጥ ምግብ ማዘጋጀት የሴቶች ብቻ ነው? ተነጋገሩበት፡፡
4. በአካባቢያችሁ የሰርግ ስነ-ስርዓት ሂደት ምን ይመስላል ተነጋገሩበት፡፡

ለ. ቀጥሎ የቀረበውን አመጋገብ አመልካች ምስል ተመልክታችሁ ሃሳቡን በአንድ አንቀጽ ተናገሩ፡፡







## ክፍል ሦስት፡- ማንበብ

### የገረፍታ ንባብ

አንድን ተፈላጊ መረጃ ብቻ ነጥለን ማውጣት ስንፈልግ የምንጠቀምበት ስልት ነው፡፡ ለምሳሌ የስም ዝርዝር፣ ስልክ ቁጥር ወዘተ.

### ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች፡፡

1. የምግብ አበላል ስርዓት ምንድ ነው?
2. ምግብ ከመመገባችሁ በፊት ምን ምን ተግባራን ትፈጽማላችሁ?
3. የተመጣጠነ የምግብ ስርዓት ማለት ምን ማለት ነው?



## የአመጋገብ ስርዓት

በእጅ የሚበላውን በእጅ፤ በሹካ የሚበላውን በሹካ፤ የማንኪያውን በማንኪያ እንዳግባቡ አጥንቶ ጠይቆ መጠቀም ነው፡፡ የሚቀርበው ምግብ ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚበላ በማየት ወይም በመጠየቅ መለየት ያስፈልጋል፡፡ ከግንዛቤ ጉድለትና በከንቱ መግደርደር የተነሳ ባለመጠየቅ ብዙ ሰዎች ለእጅ መታጠቢያ የቀረበውን ሳሙና ያለበት ለብ ያለ ውሃ እንደሾርባ ጠጥተው ሆዳቸውን አጥበዋል፡፡

ሰላጣ ላይ እንዲጨመር የቀረበን ቅመም አጠቃቀም ሳያውቁ ጨጓራቸውን የላጡም አሉ፡፡ ኮርንፍሌክስና ወተት ተለያይቶ የቀረበለት የአየር መንገድ እንግዳ መጠየቅ ነውር መስሎት ወተቷን ክልብስ አድርጎ ኮርንፍሌክሷን እንደ ድንች ጥብስ ይበላ ጀመር፡፡ ሻይ ቅጠሉንም ከነወረቀቱ ሙቅ ውሃው ውስጥ መንከር ሲገባው ወረቀቱን ቀዶ የሻዩን ቅጠል ሲበትን/ሲጨምር የታየ እንግዳ ‹‹ምነው›› ቢሉት ካፈርኩኝ አይመልሰኝ የሚል

አይነደረቅ "በኛ ሰፈር እንደዚህ ነው የሚጠጣ" ሲል መልሷል፡፡

ለስላሳ ስጋና ጣፋጭ ሾርባ ነው ብለው ጥስቅ አድርገው ከበሉ በኋላም የዝንጀሮ፣ የድመት፣ የውሻ፣ የእባብ፣ የኤሊ ስጋ/ሾርባ ነው ሲሏቸው ወደላይ ወደታች የሚጣደፉ ብዙዎች ናቸው፡፡ ትእዛዙ እንኳ "ጠይቁ ይሰጣችኋል" ነበር፡፡ ማወቅና መረዳቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ምግብ ሲቀርቡ በአግባቡ ለብሶና ጸድቶ መቅረብ ነው፡፡ ለጤናም ለእይታም የሚበጀው ለምግብ ሲቀርቡ ቀጥ ብሎ መቀመጥ ነው፡፡

የሚጎረሰው ምግብ ካለጥርጥር አፍ ውስጥ ገብቶ ያለችግር መላመጥ እንደሚችል ተደርጎ መመጠን አለበት፡፡ እንደዳረጎት ጠቅልሎ ጎርሶ አይጥ እንደዋጠ እባብ ጉንጭን ነፍቶ አይንን ማፍጠጥ አጉልኛ ነው፡፡ በቢላው እየተቆረጠ በሹካ የሚጎረስ ከሆነ በመቁረጥ ጊዜ ተፈናጥሮ የራስንም የሌላውንም ልብስ እንዳይበክል መጠንቀቅ ነው፡፡ የተቆረጠው ተጎርሶ እስኪዋጥ ቢላዋና ሹካው ሳህኑ ላይ አርፈው መቆየት አለባቸው፡፡ እንጀራ በወጥ በእጅ መበላት እንዳለበት ነው፡፡

ሌላው እንጀራ በወጥን በእጅ እንዲበላ ማስተማር አለብን እንጂ እኛ እንጀራ በወጥን በሹካ መብላት መማር የለብንም፡፡ መጠነኛ እንጀራ ተቆርሶ በመጠነኛ ወጥ ተጣብቆ መጠነኛ ጉርሻ አፍን በመጠኑ ከፍቶ አስገብቶ አፍን ዘግቶ ማላመጥ ነው፡፡ እንጥል እስኪታይ አፍን ከፍቶ ማላመጥና የሆነ እንጧ! እንጧ! የሚል ድምጽም ማሰማት ጸያፍ ነው፡፡ ምግብ አፍ ውስጥ እያለ ማውራትና መሳቅ ጸያፍ ብቻ ሳይሆን አደገኛም ነው፡፡

*ምንጭ፡- ሀብታሙ ሥዩም 17 መድፌና ሀያ ምናምን ቁምጣ 2006 ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ)*

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ**

1.እየተመገቡ ማውራት ምን ችግር ያስከትላል?
2. በእጅ  የሚበሉ ምግቦች ምን ምን ናቸው በሹካ የሚበሉ ምግቦችስ ምን ምን ናቸው
3. “ወጥና ወንድም ማስፈራሪያ  ነው” ማለት ምንን ይገልፃል?
4. ምግብ መመገብ የራሱ ሥርአት ቸለው ? መልሳቹ አዎ ከሆነ አብራሩ

**ለ.  የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልስ በጽሁፍ ስጡ፡፡**

1. በመብል ጊዜ ጸያፍ ተግባራት ተብለው የተጠቀሱት ምን ምን ናቸው?
2. ፈረሰኛና አከርካሪ የተባሉት ምንድን ናቸው?
3. ለምግብ ሲቀርቡ መደረግ አለባቸው የተባሉት ነገሮች ምንድን ናቸው?
4. ካለመጠየቅ የተነሳ በሰዎች ላይ ከደረሱ ገጠመኞች ውስጥ ሁለቱን ፃፉ፡፡

**ሐ. ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት ዓውዳዊ  ፍቺያቸውን ጻፉ፡፡**

1. ማራገፍ
2. መምጠጥ
3. አደገኛ
4. ከንቱ
5. ማላመጥ

ክፍል አራት፡- መጻፍ

**ሀ. የሚከተሉት ጥያቄዎች እንደየአጠያየቃቸው በጽሁፍ መልሱ፡፡**

1. ምግብ መመገብ ጀምረው እስከሚጨርሱ ድረስ ያለውን ሂደት ጻፉ፡፡
2. ከወላጆች ጋር መመገብ ያለውን ጠቀሜታ በአንድ አንቀፅ ግለጹ፡፡

**ለ. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች አሳጥራችሁ ጻፉ፡፡**

1. አዲስ አበባ ----------------------------------------------------------------
2. አዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ------------------------------------------------
3. ኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት----------------------------------------------------
4. ጤና ሚኒስቴር----------------------------------------------------------------
5. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ---------------------------------

**ሐ. በቀረበላችሁ ምሳሌ መሰረት ራስችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጽሁፍ ግለፁ ፡፡**

## ራስን መግለፅ

እኔ ተማሪ ገመቹ ቶልቻ እባላለሁ፡፡ የተወለድኩት ከአባቴ ከአቶ ቶልቻ ለሚሳ እና ከእናቴ ከወይዘሮ ባንቻየሁ ደበላ በ2002 ዓ.ም ባሌ ሮቤ ተወለድኩ፡፡ አሁን የምማረው በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ቡልቡላ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አምስተኛ ክፍል ነው፡፡ ሁለት እህት እና አንድ ወንድም አሉኝ፡፡ የእህቶቼ ስም አያንቱ ቶልቻ፣ ቦንቱ ቶልቻ የወንድሜ ስም ደግሞ ቀልቤሳ ቶልቻ ይባላል፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

**ሀ. በአረፍተ ነገር መሰረት ከስር ለተሰመረባቸው ቃላት ፍቺ ስጡ፡፡**

1. <u>ቤት ያፈራውን</u> ብላ፡፡

   ______________________________

2. በኑሮ ሩጫ <u>የተዋከበ</u> ነው፡፡

   ______________________________

3. <u>ማዕድ</u> ማለት ምን ማለት ነው?

   ______________________________

4. በጋራ የመብላት ባህል ገና <u>አልዳበረም፡፡</u>

   ______________________________

5. <u>ልብ ለልብ</u> መተዋወቅ አለብን፡፡

   ______________________________

6. <u>የመሻሻል አዝማሚያ</u> እያሳየ ነው፡፡

   ______________________________

## ለ. የሰንጠረዥ ጨዋታ

ምሳሌ፡- የወር ስም --- ጥር

1. ባህላዊ መጓጓዣ
2. እንቁላል የምትጥል የቤት እንስሳት
3. የወተት ተዋፅዖ
4. ቤት የሚጠብቅ
5. አይጥ የምታባርር
6. ለባህላዊ እረሻ የሚያገለግል እንስሳ
7. የዱር እንስሳት ንጉስ
8. የዝሆን ልጅ
9. የአንበሳ ልጅ
10 ታሪካዊ ዋሻ

11.የኢትዮጵያ ዋና ከተማ

12. የሰዎች መኖሪያ ቦታ

13 . የዶሮ ማደሪያ

14. የተሰበረ ሸክላ

15. የሰውን ንብረት በድብቅ የሚወስድ

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ግ | ዶ | አ | ኤ | ል | | ሞ |
| ሮ | መ | ዲ | ስ | ል | | ሌ |
| ው | ሻ | ል | አ | በ | | ባ |
| አ | አ | ደ | ቦ | ል | | ገ |
| ን | ድ | ይ | ሶ | ፍ | | ኡ |
| በ | ሬ | መ | ብ | መ | | ር |
| ሳ | መ | ሬ | ት | ቆ | | ጥ |

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ሀ. በተሰጡት አማራጮች ቀጥለው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች አሟሉ፡፡

ኢትዮጵያዊያን ሰዓሊ መስሪያ መነገኛ የተላጨው

1. ________________ፀጉር እንደገና መብቀል ጀመረ፡፡
2. ________________ ዕቃ ሳይኖረው ቤት ለመስራት ይፈልጋል፡፡
3. ________________ ገንዘብ ያስፈልጋል፡፡
4. ________________ አርበኞች ጠላትን ድል አድርገዋል፡፡
5. ________________ የጥበብ ሰው ነው፡፡

የቃላት እርባታ፡- ከአንድ ቃላት በርካታ ቃላትን መመስረት እንችላለን፡፡

**ለ. የሚከተሉት ግሶች በምሳሌ መሰረት ፃፉ፡፡**

| ሄደ | ሄደች | ሄድን | ሄዱ | ሄድሽ | ሄድክ | ሄድኩ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ተቀበለ | | | | | | |
| መታ | | | | | | |
| ሸጠ | | | | | | |
| ራቀ | | | | | | |
| ተኛ | | | | | | |
| መጣ | | | | | | |

**ሐ. በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ቃላት አስተካክላችሁ ዓረፍተ ነገሮችን በሚሟላት ፃፉ፡፡**

1. ልጁ ጫማውን በደንብ ______________________ (ማሰር)
2. ስለግል ንጽህና አጠባበቅ ________________ (ማብራራት) ተሰጣቸው፡፡
3. በሀገራችን ______________________ (መታወቅ) አትሌቶች አሉ፡፡
4. በነበራቸው የዕረፍት ጊዜ ____________________ (ደስታ) ናቸው፡፡
5. አባቴ ለእኔ ሁለት ሱሪ _____________________ (መግዛት)፡፡

መ. የሚከተለውን አንቀጽ ያለበትን የሰዋስው ስህተት አስተካክላችሁ ጻፉ፡፡

እሁድ የሳምንቱ ሰባተኛ ቀን ናቸው፡፡ ገመቹና እመቤት የዕረፍት ጊዜያችው ስለሆነ ወደ ገበያ ሄደ፡፡ አትክልት ተራ በመሄድ ስድስት ኪሎ ሽንንኩርት፣ ሦስት ኪሎ ድንች፣ አራት ኪሎ ቲማቲምና አንድ ኪሎ ቃሪያ ገዛን፡፡ ከዚያም ለልጆቻቸው ልዩ ልዩ ልብሶችን ገዘተው ወደ ቤታቸው አስመለሱ፡፡

## ክፍል ሰባት፡- ስነ-ፅሁፍ

### ሀ. ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች  አቻ ፍቺ ስጡ፡፡

| ቻይ(ተጋሽ) | ረጅም | ሰንሰለት | ተንኮለኛ | ጠበቃ |
|---|---|---|---|---|

1. ብቅል አውራጅ ____________________
2. ነገረ ፈጅ ____________________
3. እግረ ሙቅ ____________________
4. ሆደ ሰፊ ____________________
5. መሰሪ ____________________

### ቃላዊ ግጥም

ሰዎች የተለያያ ስራ ላይ ሲሰማሩ፣ ይብለጥ የጉልበት ስራ በሚሰሩበት ወቅት ድካም እንደይሰማቸው የሚያዜሙት፣ የሚጠይቁበት እና ተዝናናቶ የሚፈጥሩበት ነው፡፡ አይነቱም፡- የስራ፣ የፍቅር፣ የሙሾ፣ የልመና፣ የክብረ በዓል፣የሰርግ፣ የቀረርቶ፣ በላ ልበልሃ ወዘተ ናቸው፡፡ (ፍኖት 82፣2013ዓ፣ም)

ለምሳሌ፡- በእርሻ ወቅት

የመጋል ጌታ የስመጥሩ

የጋሬ ጌታ የሰመጥሩ

የጆሮ ጌታ የሰመጥሩ

መብረቅ ያረሰው ይመስላል ፈሩ፡፡

### ለ. በአካባቢያችሁ በተለያዩ በዓላት ከሚቀርቡ ስነ ቃሎች ውስጥ የምታውቁትን ክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡

ለምሳሌ ሰርግ ፣ ለቅሶ፣ ጥምቀት፣ አረፋ

## ክለሳ ጥያቄዎች

ሀ. ከዚህ ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች በትዕዛዙ መሰረት መልስ ስጡ፡፡

1. በአካባቢያችሁ የሚኖሩ ሰዎችን ስለ  እቁብ ፡-
    1.1 የእቁብ አባላትን አደረጃጀት፣
    1.2 የእጣ አወጣጥ ስርዓት፣
    1.3 የገንዘብ አከፋፈል ስርዓትና
    1.4 ማጠናቃቂያ ስርዓት ጠይቃችሁ ሃሳቡን በአንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለክፍል ገደኞችሁ አቅርቡ፡፡

2. የገርፍታ ንባብ የሚባለው ምን አይነት ንባብ ነው ተወያያታችሁበት ለክፍል ጓደኞችሁ አቅርቡ፡፡

3. ቤተሰብ በጋራ መመገብ የሚያስገኛውን ጠቀሜታ ተናገሩ፡፡

ለ. በሚከተሉት ቃላት ነጠላ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

1. ትምህርት
2. ሕጻናት
3. ቋንቋ
4. መሰረት
5. ማፍለቅ

ሐ. ሚና ተከፋፍላችሁ ማጥናት የሚወድ ተማሪና ማጥናት የማይወድ ተማሪ መካከል የሚደረግ ምልልስ አድርጉ፡፡

መ. ቆይተው የተገናኙ ጓደኛሞች ሲገናኙ የሚለዋወጡትን ሰላምታ እንዲሁም ስለነበሩበት ሁኔታ ሃሳብ ሲለዋወጡ የሚያሳይ ሁኔታ በተግባር አሳዩ፡፡

| | ሙዳይ ቃላት |
|---|---|
| 1. ሄፓታይተስ | የጉበት በሽታ አይነት |
| 2 . መበከል | መመረዝ |
| 3. .ሟሸሸ | ሟሟ |
| 4. . ፋሽስት | ወራሪ/ ጠላት/ |
| 5. . አርበኛ | ሀገርወዳድ /ጀግና/ |
| 6. ጠመደው | ለእርሻ ስራ አዘጋጀው |
| 7 .መከሰት | በድንገት መታየት |
| 8 . የተጸውዖስም | የአንድ ሰው ወይም ነገር መጠሪያ ስም |
| 9 . የወል ስም | የተመሳሳይ ነገሮች መጠሪያ |
| 10 . የረቂቅ ስም | የማይዳሰሱ የማይታዩ ነገሮች መጠሪያ |
| 11 .የጥቅል ስም | የብዙ ነገሮች የጋራ መጠሪያ |
| 12 . አፈርሳታ | ባህላዊ የጠፋ ንብረት ማስመለሻ |
| 13 . ቅርስ | ሀብት |
| 14 ጎብኚ | ተመልካች |
| 15 . ግብር | ከግል ገቢ ለምግስት የሚከፈል ገንዘብ |
| 16 . ጎዳና | መንገድ |
| 17 . ክርክር | ሙግት |
| 18 . ሚና | ድርሻ |
| 19 . በጋራ | በኅብረት |
| 20. ቅስፈታዊ | ድንገተኛ |
| 21. ቅዠት | ህልም |
| 22 .ትዕይንት | ድርጊት |
| 23. .ሀገር በቀል | ሀገራዊ የሆነ / በሀገር ውስጥ የሚገኝ/ |
| 24. ኅብረት | አንድነት |
| 25. ታካች | ስልቹ |
| 26. ረብ | ጥቅም |

| | |
|---|---|
| 27. መድብል | ስብስብ |
| 28. ግንጣይ | ክፋይ |
| 29. አሜኬላ | እሾህ/ክ/ |
| 30. ነፃ ምእላድ | ትርጉም አዘል ቃል |
| 31. ጥገኛ ምእላድ | ተግባር ያለው ትርጉም የሌለው |
| 32. ኢ -ልቦለድ | እውነተኛ ታሪክ |
| 33. ቅጥያ | በዋና ቃል ከፊት ወይም ከኋላ የሚጨመር |
| 34. ቀደምት | ድሮ/ጥንት/ |

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

2014 ዓ.ም